bible educational services

# የመምህሩ መምሪያ

## የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ደረጃ 3 እና 4

ተከታታይ ትምህርቶች 7-12

www.besweb.com

# የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት
በሕግ የተመዘገበ የዩናይትድ ኪንግደም ለጋሽ ድርጅት (የምዝገባ ቁጥር 1096157)

**ተልእኮ**
በአለም ዙሪያ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ እንዲሁም በዚህ ዘመን ያለውንና የወደፊቱን ትውልድ የእግዚብሔርን ቃል ለማስተማር የሚረዱ ተከታታይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በማዘጋጀት ሰዎችን ማገልገልና ለአገልግሎት ብቁ ማድረግ።

**ራዕይ**
የተለያዩ የኮሙኒኬሽን አይነቶችን ስራ ላይ በማዋልና ዋና ዋና እሴቶቻችን ከሚጋሩ ግለሰቦች ጋር አብሮ በመስራት በተለየዩ የዓለም ቋንቋዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ዝግጅትን ማበረታታት።

## አጠቃላይ መረጃ

**የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ተግባራት ምንድናቸው?**

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት "ዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ"፣ "አዲስ ሕይወት" እና "ቃራሚዎች" በሚል ርዕስ የሚታወቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በእንግሊዝኛ ያሳትማል። እንዲሁም በምድረ እንግሊዝና በሌሎች የዓለም ክፍሎች በፖስታ ቤቶች አማካኝነት በመላላክ እነኝህን ትምህርቶች የሚሰጡ የርቀት ትምህርት ቤቶችንና ሌሎች ድርጅቶችን በጉብኝት፣ በምክር፣ በኔትወርኪንግና በስልጠና ያግዛል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት በአሁኑ ጊዜ በትርጉም፣ በዲዛይን፣ በሕትመትና ትምህርቶችን በማሰራጨት ከሚሰሩና በሌሎች አገሮች ውስጥ ከሚገኙ ቡድኖች ጋር አብሮ ይሰራል። ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርቶቹ በነፃ እንዲዳረሱ ማድረግም ሌላው የመጽሐፍ ትምህርቶች አገልግሎት ተግባር ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቶች በመጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉት በደቡብ አየርላንድ ከ50 ዓመታት በፊት ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት በእንግሊዝኛና በሌሎች የውጭ አገር ቋንቋዎች የሚዘጋጁ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን የኤዲቶሪያል ኃላፊነት ይወስዳል። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ሕትመት በኤ 4 ፎርማት ሆኖ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚገኙ ተማሪዎች በአራት ሳምንት አንድ ጊዜ ትምህርቶችን ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ማዕከል ለእርማት መላክ እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለቤት ለቤት ጀማ ወንጌል (የተሐድሶ ንቅናቄ) ምስጋና ይግባውና በቤልፋስት የ6 ወራት ትምህርቶች በኤ 5 ፎርማት ማዘጋጀት ተችሏል። ይህም ትምህርቶች በት/ቤቶችና በየአብያተ ክርስቲያናቱ በቀላሉ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አስችሏል። ይህ ደግሞ ጥሩ የፖስታ አገልግሎት በሌለባቸው አካባቢዎች ውጤታማ ሆኗል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ኮርሶችን ልዩ የሚያደርጋቸው የቤት ለቤት ወይንም ደግሞ በቤተ ክርስቲያንና በት/ቤቶች የሚካሄዱ የቡድን ጥናቶችን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተውና በሚገባ የታቀደ ሲለበስን ተከትለው ተማሪዎች ጥናታቸውን እድሜያቸው 20 ዓመት እስኪሆነው ድረስ እንዲቀጥሉ ስለ ሚረዷቸው ነው። ለየእድሜ ደረጃው የሚመጥኑ በአምስት ደረጃዎች የተከፋፈሉ ትምህርቶች ቀርበዋል። ቅድመ መደበኛ ትምህርት፣ ከ5-7 ዓመት፣ ከ8-10 ዓመት፣ ከ11-13 ዓመት፣ ከ14-16 ዓመት። ለእያንዳንዱ የእድሜ ክልል የሶስት ዓመት ሲለበስ ተዘጋጅቷል። (ገፅ አራትን ይመልከቱ።) እያንዳንዱ የእድሜ ክልል ባሉት ችሎታዎች መሠረተ ይለያያል። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ልጆች የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያጠኑ እድል ይፈጥርላቸዋል። ይህም የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን እንዲማሩና ወንጌልን በሕይወታቸው ለመተግበር በሚያደርጉት ጥረት የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች መጋፈጥ እንዲችሉ በማገዝ ነው።

የእነኝህ ትምህርቶች ኮፒዎች በእንግሊዝኛ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ዌብ ሳይት **(www.besweb.com) ላይ** ማውረድ ይቻላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት አብረውት በአጋርነት መስራት ለሚፈልጉ ሰዎች የሚጠቅሙ ዶክሜንቶች አሉት። እነኝህ ዶክሜንቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ዌብ ሳይት ላይ ይገኛሉ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት አድራሻዎች

**ዓለም አቀፍና የሰሜን አየርላንድ ፀሐፊ (የሁሉም ትምህርቶች አከፋፋይ)**
Mr S Balmer, 37a Belmore Street, Enniskillen, Northern Ireland BT74 6AA
ስልክ: 0286 632 2462
ኢሜይል: sam@besweb.com

**የዩናይትድ ኪንግደም ፀሐፊ**
Mr Stephen Gillham, 32 Firs Glen Road, West Moors, Ferndown, Dorset BH22 0ED
ስልክ: 01202 873500
ኢሜይል: stephen@sgilllham.co.uk

**ዌብ ሳይት**: www.besweb.com
**የኢሜይል አድራሻ**: info@besweb.com

## ለመምህራን መምሪያዎች

የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች በመጀመሪያ ሲዘጋጁ በፖስታ በመላላክ ለማስተማር ታስበው ነበር። ለዚህም ይረዳ ዘንድ የፖስታ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ማዕከላት ተቋቁመው ነበር። ነገር ግን የፖስታ አገልግሎት አስተማማኝ ባልሆነባቸው እስከጭራሹንም እየቀረ በሚሄድባቸው ስፍራዎች በተለይም ደግሞ በአፍሪካና በሕንድ እንዲሁም በሌሎች የዓለማችን ክፍሎች በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለሚጠቀሙ የማስተማሪያ መምሪያዎችም ተዘጋጅተዋል። በዚህ ጥራዝ ውስጥ የተዘጋጁት የመምህሩ መምሪያዎች ታሳቢ ያደረጉት ደረጃ 3 እና 4ን በግምት እድሜያቸው ከ11-14+ ዓመት የሆኑ ልጆችን ነው።

እያንዳንዱ የመምህሩ መምሪያ ልክ ***በዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ*** ትምህርት ውስጥ የተጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ተከትሎ የተዘጋጀ ነው። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችና መምሪያዎቻቸው በየሳምንቱ እንዲጠኑ ተደርገው ተዘጋጅተዋል። የሚያዚያ ትምህርቶች በተለይ ከፋሲካ ጋር የተገናኙ ትምህርቶች ሲሆኑ የታህሳስ ትምህርቶች ደግሞ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጋር የተገናኙ ናቸው።

በአንዳንድ ቦታዎች በኤ 4 የወረቀት መጠን የሚዘጋጀውን ሳምንታዊ ሕትመት ሲጠቀሙ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ 24 ትምህርቶችን የያዘውንና በኤ 5 የወረቀት መጠን የተዘጋጀውን ጥራዝ ይጠቀማሉ። መምህሩ ወይንም ደግሞ የጥናቱ/የትምህርቱ መሪ በኤ 4 የወረቀት መጠን ትምህርት ያድላል። ትምህርቱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወይንም ደግሞ በት/ቤት ይሞላል ወይንም ደግሞ ወደ ቤት ይወሰዳል። ከዚያም በተከታዩ ሳምንት ይመለሳል። በወሩ መጨረሻ መምህሩ ወይንም የጥናቱ/የትምህርቱ መሪ ትምህርቶችን ይሰበስብና ያርማቸዋል። ነጥብም ይሰጣቸዋል። በተቻለ መጠንም ከእርማት በኋላ ለተማሪዎች መመለስ አለበት።

የተዘጋጁት ጥራዞች ጥቅም ላይ ከዋሉ በየሳምንቱ መጨረሻ እየተሰበሰቡ ይታረማሉ። በብዙ ምክንያቶች ይህ አስቸጋሪ እንደሆነ እንረዳለን። ስለዚህም በክፍል ውስጥ ጥራዞቹ ለተማሪዎች ይከፋፈላሉ። በዚህ ጊዜ መምህሩ/መሪው ከተማሪዎች ጋር አብሮ ይሰራል። ተማሪዎችም የጓደኞቻቸውን ስራዎች ያርማሉ፣ ነጥብም ይሰጣሉ። ከጥራዞቹ በስተጀርባ ለእያንዳንዱ ነጥብ መመዝገቢያ ሰንጠረዥ እንዲሁም ተማሪው ስላሳየው እድገት አስተያየት መስጫ ቦታ አለ። እንዲሁም ከጥራዙ በስተመጨረሻ ሰርተፊኬት ተያይዟል። ይህ ሰርተፊኬት በቀላሉ ከጥራዙ ላይ ሊገነጠል የሚችል ሲሆን ተማሪው ባለፉት 6 ወራት ከመቶ ያገኛቸውን ውጤቶች ይይዛል።

## ለመምህራን የተደረገ ዝግጅት

*መምህራን በራሳቸው ዘዴ ወይንም መንገድ፣ ተነሳሽነትና ሀሳብ ላይ የተመሠረተ አንዳችም ነገር እንዲያደርጉ አንጠብቅም። ለእንደዚህ አይነት ጉዳይ ምንም ቦታ አንሰጥም። የሚከተሉት ሀሳቦች የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ጠቃሚ ሀሳቦች ናቸው።*

- ***ከታሪኩ ጋር በሚገባ ራስን ማስተዋወቅ*** - *ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችና በተጓዳኝ አብረውት ከሚሄዱት የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ጋር በተቻለ መጠን ራሳቸውን ማስተዋወቅ አለባቸው። መምህሩ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ከማስተማሩ በፊት ራሱ አጥንቶ ቢያጠናቅቅ ተመራጭ ነው። ለእያንዳንዱ ትምህርት የተዘጋጁት መምሪያዎችም በእቅድ ወቅት ስለ ሚረዱ በጥንቃቄ ሊታዩ ይገባል።*
- ***ትምህርቶችን በሚገባ መረዳት*** - *ከእያንዳንዱ የትምህርት እቅድ በላይ “በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።” የሚሉ ቃላት ይገኛሉ። እነኝህም መምህሩ ገለፃውን ካጠናቀቀ በኋላና ተማሪዎችም ያንን የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከተማሩ በኋላ የሚጨብጧቸውን ሁለት አላማዎች የያዙ ናቸው። የመጀመሪያው አላማ ከታሪኩ ስለ ቀሰሙት እውቀት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎች ስላገኙት እውቀት እንዲያሰላስሉና በተቻለ መጠንም ምላሽ እንዲሰጡና ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱት ያበረታታል። እነኝህ የመማር አላማዎች በተሰጠው ትምህርት ውስጥ ያለውን ዋና ፅነሰ ሀሳብ/እውነት የያዙ ናቸው። መምህራንም ራሳቸውን እንዲሁም የመማር የማስተማር ሂደቱን ለመገምገም ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።*
- ***አስተዋውቁት/መግቢያ*** - *ሁሉንም ትምህርቶች የምንጀምረው ከራሳቸው ከተማሪዎች ልምምድና ካሉበት ሁኔታ በመነሳት ነው። ታሪኮችን በመግቢያው ውስጥ ለማስተዋወቅ የተለያዩ ዘዴዎችን አቅርበናል። በዚህም ልጆች በትምህርቱ ማስጀመሪያ ነጥብ ላይ በመስተጋብር የተሞላ ውይይት እንዲያካሂዱ እናስችላቸዋለን።*
- ***የማስተማር ጊዜ*** - *የታሪኩን ቁልፍ ነጥቦች አቅርበናል። መምህራን ታሪኮቹን በሚያስተምሩበት ወቅት እነኝህን ቁልፍ ነጥቦች እንደማያነሷቸው ተስፋ እናደርጋለን። ሆኖም በሚያስምሩበት ወቅት ራሳቸውን ከታሪኩ ጋር በሚገባ አስተዋውቀው ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተማር ይጠቀሙባቸዋል። መምህሩ በትምህርቱ ውስጥ ያለውን ታሪክ ተማሪዎቹ በሚገባ እንዲረዱ ማድረግ አለበት። እንዲሁም ልጆቹ ታሪኩን ከተገነዘቡት በኋላ መስጠት ስላለባቸው ምላሽ አቅጣጫ ይጠቁማቸዋል። ከእያንዳንዱ ትረካ ጋር አብሮ የሚሄዱ ማብራሪያዎችንም አብረን ማቅረቡ ተገቢ ስለሆነ ይህንኑ አድርገናል። እነኝህም በኢታሊክስ (ITALICS) ተፅፈው ቀርበዋል።*
- ***የመማር ጊዜ*** - *ከእያንዳንዱ ታሪክ ጋር አብሮ የተያያዘ ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አለ። አንዳንድ ጊዜም ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተያይዘዋል። ምክንያቱም ተጨማሪው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተማሪዎች በቀላሉ መማር እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ልጆች እነኝህን ቁልፍ ጥቅሶች እንዲማሩ እንዲሁም በተደጋጋሚ እንዲያስታውሱት እንደሚደረግ ተስፋ እናደርጋለን። ይህም ልጆች የቁልፍ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እውቀት ግንባታ ማድረግ እንዲጀምሩ ይረዳቸዋል።*
- ***ማጠናቀቅ*** - *በት/ቤት ውስጥ ተማሪዎች ሰርቶ ማሳያ/የመለማመጃ ጥያቄዎችን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጋቸውን የችሎታ ልክና መምህሩ በዚህ ረገድ ለተማሪዎቹ ሊያደርግላቸው የሚችለውን የእገዛ መጠን በተመለከተ ግንዛቤ ሊኖራችሁ ይገባል። አንዳንዶች መምህሩ ታሪኩን ካነበበላቸውና ከታሪኩ ጋር በሚገባ ከተዋወቁ በኋላ ወደ ስራ ይገባሉ። ሌሎች ልጆች ደግሞ ታሪኩን ራሳቸው ማንበብ ይችላሉ። በሁለቱም መንገዶች ዋናው ሀሳብ ጥያቄዎቹን ለመስራት በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ የልጆቹ አትኩሮት እንዲያርፍ ማድረግ ነው። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ከት/ቤት ውጪ በሌሎች ቦታዎች የምትጠቀሙ ከሆነ ተማሪዎቻችሁን ባሉበት ቦታ በአካል ተገኝታችሁ መርዳት መቻል አለባችሁ። አለበለዚያ ተማሪዎቻችሁ ትምህርቱን እንደፈተና ወይንም ደግሞ የግድ መጠናቀቅ እንደላበት ስራ አድርገው ሊቆጥሩት ይችላሉ። አስደሳች መሆን አለበት። ለዚህም ተማሪዎች እየሰሩ ባለበት ወቅት ማበረታታት አስፈላጊ ነው።*
- ***የክለሳ ጊዜ*** - *በተቻለ መጠን ተማሪዎች በምን ያህል መጠን ትምህርቱን አውቀውታል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚረዱንን አጫጭር ሙከራዎችን መስጠት ወይንም አስፈላጊ መሆኑን እንመክራለን። ይህም ትምህርቱን ለመከለስና የተማሪዎችን የመማር ፍጥነት ለማገዝ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።*
- ***ማሳየት*** - *በአንዳንድ ሁኔታዎች የቪዥዋል (የእይታ) ትምህርት መርጃዎች በቀላሉ ላይገኙ ቢችሉም በተቻለ መጠን ለሚታዩ ስዕሎች ወይንም ደግሞ ለሌሎች ቁሳቁሶች ትኩረት መስጠትና በተግባር ማዋል ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ይረዳቸዋል።*

በትረካ ወቅት የእይታ ትምህርት መርጃዎች ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ። አስፈላጊ የሆኑ ስዕሎችን በተመለከተ መረጃ ከተፈለገ ከሚከተለው ዌብ ሳይት ማግኘትና ስዕሎችንም ማውረድ ይቻላል። [www.freebibleimages.org (FBI)] ሌላው የእይታ መርጃዎችን የምናገኝበት ምንጭም Eikon Bible Art [info@eikonbibleart.com] ዌብ ሳይት ነው። ሆኖም ከዚህ ዌብ ሳይት የምናገኛቸው ምንጮች በሽያጭ የሚገኙ ናቸው። የፎቶ ኮፒ ማሽን ባለበት አንዳንድ ስእሎች ሊተልቁ ቀለም ሊቀቡና በትምህርት ወቅት ጥቅም ላይ ማዋል ሊውሉ ይችላሉ።

**ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የማስተማር ጊዜ**

1) ጥቅሱ በወረቀት ወይንም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ሊፃፍ ይችላል። ይህም የተለያዩ ቃላትን በማጉደል የሚደረግ ነው። ይህም ሁሉም የጥቅሱ ቃላት በሙሉ እስኪነሱና ተማሪዎችም ጥቅሱን በቃላቸው መድገም እስኪችሉ ድረስ ነው።
2) ቁልፍ ጥቅሱን ለማስተዋወቅ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ።
   ሀ) በሁለት ቡድኖች መስራት (በገመድ የመስቀል ዘዴ) – የቁልፍ ጥቅሱ የተለያዩ ፊደላት ተቀንሰው በምትካቸው ክፍት ቦታዎች አሉ። ልጆችም የትኞቹን ቃላት ቢጠቀሙ ጥቅሱን ማሟላት እስከሚችሉ ድረስ ይሰራሉ። ይህም ከመካከላቸው አንደኛው ልጅ ጥቅሱን እስከሚለየው ድረስ ይቀጥላል።
   ለ) ጥቅሱን ቀድሞ መፈለግ። መጽሐፍ ቅዱስ በቀላሉ የሚገኝ ከሆነ ተማሪዎች ቁልፍ ጥቅሱን ይፈልጋሉ። መጀመሪያ ጥቅሱን ያገኘው ልጅ አሸናፊ ይሆናል።

**ጊዜን ማቀድ**

- **ቅደም ተከተል** ለሁሉም የማስተማሪያ መምሪያዎች ተመሳሳይ ቅደም ተከተል እንጠቀማለን። ሆኖም ይህን ቅደም ተከተል መምህራን እንደአስፈላጊነቱ ሊቀያይሩት ይችላሉ።
  - o መግቢያና ትረካ - በግምት 15 ደቂቃ
  - o ቁልፍ ጥቅሱን የማስተማር ጊዜ – ከ5 እስከ10 ደቂቃ
  - o ስርቶ ማሳያውን ማጠናቀቅ - 20 ደቂቃ
  - o መልመጃና ሌሎች ስራዎች 5-10 ደቂቃ

ይህን አባባል ሁሌም አስታውሱት።

“የነገራችሁኝን እረሳለሁ።
የምታሳዩኝን አስታውሳለሁ።
አብሬያችሁ ስሰራ በሚገባ እረዳለሁ።”

## የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ሲለበስ

| | ደረጃ 0 (ቅድመ መደበኛ ትምህርት)<br>ደረጃ 1 (ከ5-7 ዓመት)<br>ደረጃ 2 (ከ8-10 ዓመት) | ደረጃ 3 (ከ11-13 ዓመት) | ደረጃ 4 (14 ዓመትና ከዚያ በላይ) |
|---|---|---|---|
| የጀማሪዎች ተከታታይ ትምህርቶች | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. ሀ1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. ሀ1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. ሀ1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል |
| ሀ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. አብርሃም<br>6. አብርሃም<br>7. ጴጥሮስ<br>8. ጴጥሮስ<br>9. ያዕቆብ<br>10. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. ጴጥሮስ<br>6. አብርሃም<br>7. ያዕቆብ<br>8. ፀሎት<br>9. ጳውሎስ<br>10. ጳውሎስ<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ፍጥረትና ውድቀት<br>2. ዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ክንዋኔዎች<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. ጴጥሮስ<br>6. አብርሃም<br>7. ያዕቆብ<br>8. የክርስቲያን ሕይወት<br>9. ጳውሎስ<br>10. ጳውሎስ<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |
| ለ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. የክርስቶስ የቀደመው ሕይወቱ<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. ምሳሌዎች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ምሳሌዎች<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የወንጌል ፀሐፊዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ምሳሌዎች<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>6. ያዕቆብና ቤተሰቡ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የሐዋርያት ስራ 2፡42 ከፊት ለፊት ያለው መንገድ<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሕግ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |
| ሐ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. ዳንኤል<br>2. ተጨማሪ ተአምራት<br>3. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩትና ሳሙኤል<br>6. ዳዊት<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. ዮናስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>3. ተጨማሪ ተአምራት<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩት<br>6. ሳሙኤል<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. እግዚአብሔር የተጠቀማባቸው የብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. የኢየሱስ አባባሎች<br>3. የጌታ ኃይል<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩት<br>6. ሳሙኤል<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. ተጨማሪ የብሉይ ኪዳን ባሕርያት<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |

| | ሀ7 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 – የያዕቆብ ሕይወት<br>ርዕስ – አታላዩ | ሀ7– ደረጃ 4<br>ጥናት 1 – የያዕቆብ ሕይወት<br>ርዕስ – አታላዩ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: *ዘፍጥረት 25: 21-34 እና ዘፍጥረት 27: 1-29*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** *መዝሙር 32: 1*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ኃጢአት ስንሰራ እግዚአብሔር ይቅር ሊለን ይችላል።<br>2. እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ይቅር ሊባርከን ይፈልጋል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: *ዘፍጥረት 25: 19-34 እና ዘፍጥረት 27: 1-41*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** *ሮሜ5: 8*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ማጭበርበርና መዋሸት ደስታችንን አርቆ ሁከትን በሕይወታችን ይሞላል።<br>2. እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው እንያዕቆብ ላለ ሰው እንኳን ሳይቀር እቅድ አለው። |
| መግቢያ | መፈተን ምን ማለት እንደሆነ ተወያዩበት። እንዲሁም እንድንዋሽ የሚፈትኑን ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ ተወያዩባቸው። እነኝህን ሁኔታዎችና ለምን እንደምንዋሽ ዘርዝሯቸው። እንዲሁም ስለመቅናትና እንድነቀና ስለሚያደርጉን ሁኔታዎች እንዲሁም ለምን እንደምንቀና ተነጋገሩበት። | ከማንኛውም ድርጊታችን ውጤት ጋር አብረን መኖር ግዴታችን ነው። ይህን ከየግል ሕይወታችን ጋር እናዛምደው። ለምሳሌ እናንተ ወይንም አንድ የምታውቁት ሰው ችግር ውስጥ የወደ ቃችሁበትን ጊዜ አስታውሱ። ምናልባትም በመዋሸታችሁና በማጭበርበራችሁ ምክንያት በፖሊስ ተይዛችሁ ሊሆን ይችላል። ወንጀል/ኃጢአት ለምን መቀጣት እንዳለበት አስቡ። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ይስሐቅ ከጸለየ በኋላ ርብቃ መንታ ልጆች ወለደች። ኤሳው ታላቁ ልጁ ሲሆን ያዕቆብ ደግሞ ትንሹ ልጁ ነው።<br>2. በቤት ውስጥ መድልዎ ነበር። ይስሐቅ ኤሳውን ሲወድ ርብቃ ደግሞ በቤት መዋል የሚወደውን ያዕቆብን ትወድ ነበር።<br>3. *በጥንታዊ መካከለኛ ምስራቅ ብኩርና የነበረውን ጥቅም ግለጹላቸው።*<br>4. ኤሳው ለአደን ወጥቶ ነበር የዋለው። እናም በጣም ተርቦ ነበር። ያዕቆብ ወጥ እያበሰለ ነበር። ለተራበው ለወንድሙ ኤሳው ከዚህ ካበሰለው ምግብ የሚሰጠው ብኩርናውን ለእርሱ ሊሰጠው ከፈቀደ ብቻ ነበር።<br>5. ይስሐቅ ሲያረጅ ለታላቅ ልጁ በረከት ሊሰጠው ፈለገ። ርብቃና ያዕቆብ ግን አይኑ ፈዝዞ ማየት እየተሳነው የነበረውን ይስሐቅን ለማታለል አሴሩ። ኤሳው ለአባቱ የሚወደውን ወጥ አዘጋጅቶ ለመስጠት እንዲችል አደን ወጥቶ በነበረበት ወቅት ርብቃና ያዕቆብ በፍጥነት ምግብ አዘጋጁ። ያዕቆብ ኤሳውን እንዲመስል ተደረገ። ስለዚህም ከአባቱ ለታላቁ ልጁ ያዘጋጀውን በረከት ተቀበለ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አንድን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ይስሐቅ ከጸለየ በኋላ ርብቃ መንታ ልጆች ወለደች። ኤሳው ታላቁ ልጁ ሲሆን ያዕቆብ ደግሞ ትንሹ ልጁ ነው።<br>2. በቤት ውስጥ መድልዎ ነበር። ይስሐቅ ኤሳውን ሲወድ ርብቃ ደግሞ በቤት መዋል የሚወደውን ያዕቆብን ትወድ ነበር።<br>3. *በጥንታዊ መካከለኛ ምስራቅ ብኩርና የነበረውን ጥቅም ግለፁላቸው።*<br>4. ኤሳው ለአደን ወጥቶ ነበር የዋለው። እናም በጣም ተርቦ ነበር። ያዕቆብ ወጥ እያበሰለ ነበር። ለተራበው ለወንድሙ ኤሳው ከዚህ ካበሰለው ምግብ የሚሰጠው ብኩርናውን ለእርሱ ሊሰጠው ከፈቀደ ብቻ ነበር። ያዕቆብ በዚህ ድርጊቱ በጣም ራስ ወዳድና ተንኮለኛ መሆኑን አስመሰከረ።<br>5. ይስሐቅ ሲያረጅ ለታላቅ ልጁ በረከት ሊሰጠው ፈለገ። ርብቃና ያዕቆብ ግን አይኑ ፈዝዞ ማየት እየተሳነው የነበረውን ይስሐቅን ለማታለል አሴሩ። ኤሳው ለአባቱ የሚወደውን ወጥ አዘጋጅቶ ለመስጠት እንዲችል አደን ወጥቶ በነበረበት ወቅት ርብቃና ያዕቆብ በፍጥነት ምግብ አዘጋጁ። ያዕቆብ ኤሳውን እንዲመስል ተደረገ። ስለዚህም ከአባቱ ለታላቁ ልጁ ያዘጋጀውን በረከት ተቀበለ።<br>6. *የማታለልን ምሳሌና የታማኝነትን አስፈላጊነት ተወያዩባቸው።*<br>7. ኤሳው ከአደን ሲመለስ እጅግ ተቆጥቶ ነበር። አባቱንም እንዲባርከው አጥብቆ ለመነው። ሆኖም በጣም የዘገየ ልመና ነበር። ብኩርናውንና በረከቱን አጣ።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አንድን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | በዚህ ትምህርት ውስጥ ያዕቆብ ስለ ፈጸማቸው ኃጢአቶች አስቡ። ስለየትኛው ኃጢአታችን ነው እኛስ ይቅርታ ልንቀበል የሚገባን? *መጀመሪያ* በጋራ አስቡ። ከዚያም በግል አስቡበት።<br><br>የሁሉንም ተማሪዎች መልሶች የምትፅፉበት ወረቀት አዘጋጁ። እግዚአብሔርን ምናልባትም ሌሎች ሰዎችን እንዴት ይቅርታ መጠየቅ እንደምንችል አስቡ። ለዚህ ይርዳችሁ ዘንድ ***መዝሙር 32: 1-5 አንብቡ።*** | ኤሳው የወንድሙንና የእናቱን ማጭበርበርና ውሸት ሲረዳ ምን ሊሰማው እንደሚችል አስቡ።<br><br>በማጭበርበራችሁና በመዋሸታችሁ ችግር ውስጥ የወደቃችሁበትን ጊዜ አስታውሱ። ወደ ፊት በተለየ አኳኋን ለመኖር የምትችሉባቸውን ሁለት መንገዶች ጻፉ። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>የፈጸማችኋቸውን አንዳንድ ኃጢአቶች በወረቀት ላይ ጻፏቸው። ወረቀቱን ከቆራረጣችሁት በኋላ በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ውስጥ ጣሉት ወይንም በወረቀት ማድቀቂያ ውስጥ አስቀምጣችሁ አድቅቁት። በአማራጭ አንዳንድ ኃጢአቶቻችሁን በአሸዋ ላይ ወይንም በአቧራማ መሬት ላይ ከጻፋችሁ በኋላ ከኋላ ወደፊት ጥረጓቸው። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. እግዚአብሔር ለያዕቆብና ለእናንተም በሕይወታችሁ ስላለው እቅድ በኤርምያስ 29፡11 ውስጥ ባለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሀ ላይ ተመስርታችሁ አስቡ።<br>2. እግዚአብሔር ስለ ወደፊት ሕይወታችሁ እንዲያሳያችሁ ጋብዙት። ቀና አስተሳሰብን አንጸባርቁ። |

| | ሀ7 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 – የያዕቆብ ሕይወት<br>ርዕስ – ሕልመኛው | ሀ7 – ደረጃ 4<br>ጥናት 2 - የያዕቆብ ሕይወት<br>ርዕስ – ሕልመኛው |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***ዘፍጥረት27: 41-46 እና ዘፍጥረት28: 10-22***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘፍጥረት28: 16***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ምንም እንኳን ያዕቆብ ቢሳሳትም እግዚአብሔር አሁንም ከእርሱ ጋር ነው። አሁንም በጣም ይወደዋል።<br>2. ለእኛም ይህ እውነት ነው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***ዘፍጥረት27: 41-46 እና ዘፍጥረት28: 1-22***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘፍጥረት28: 16***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ምንም እንኳን ያዕቆብ ነገሮችን ቢያበላሽም ለሕይወቱ ብዙ የተስፋ ቃሎችን ከሰጠው ከእግዚአብሔር ጋር አስደናቂ የመገናኘት አጋጣሚዎችን አግኝቷል።<br>2. እግዚአብሔር ልክ ለያዕቆብ እንዳደረገለት ለእኛም ያደርግልናል። |
| መግቢያ | ምንም አይነት ነገር ብናደርግም እግዚአብሔር ሕይወታችንን እንደሚቆጣጠር አስተውሉ። ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነት ልናደርግባቸው ስለምችልባቸው መንገዶች አስቡ። እንደዚሁ ሁሉ እግዚአብሔር እኛን በተለያዩ መንገዶች ሊናገረን እንደሚችል አስቡ። ተማሪዎቻችሁን ዛሬ እግዚአብሔር እኛን ሊናገርባቸው ስለሚችልባቸው መንገዶች ጠይቋቸው። | ተማሪዎቻችሁን በእግዚአብሔር እምነት ስለነበረውና በጣም አስገራሚ መለኮታዊ ተአምር በሕይወቱ ስላለፈበት አንድ ሰው ልምምድ እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው። እንዲህ አይነት ነገሮች በሕይወታችን ያልፉ ዘንድ ፍፁም መሆን አለብን? |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ከአባቱ ሞት በኋላ ኤሳው ያዕቆብን ስለመግደል ያስብ ነበር። ርብቃም የኤሳው ቁጣ እስኪበርድ ድረስ ያዕቆብ ወደ አጎቱ ላባን እንዲሄድና በዚያ እንዲቆይ አሰበች።<br>2. ይስሐቅ ያዕቆብን ባረከው። ያዕቆብም ወደ ፓዳን አራም ተጓዘ።<br>3. ያዕቆብ ሌሊት አረፈ። ሕልምንም አየ። ወደ ሰማይ የሚደርስ መሰላል አየ። እግዚአብሔርም ተናገረው። ዘሩ ስለሚወርሰው ምድርም የተስፋ ቃል ሰጠው። በጉዞም ከእርሱ ጋር እንደሚሆን አረጋገጠለት።<br>4. ያዕቆብም ከእንቅልፉ ነቃ። ያን ቦታም ቤቴል ብሎ ጠራው። ትርጉሙም የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው።<br>5. ያዕቆብ ለእግዚአብሔር ስዕለትን ተሳለ። እግዚአብሔር የሚጠብቀው ከሆነ እግዚአብሔርን አምላኩ እንደሚያደርግ።<br>6. ከያዕቆብ የቤቴል ቆይታ ልንማር ስለምንችለው ትምህርት ተወያዩ።<br>7. እግዚአብሔር ለያዕቆብ ስላለው ፍቅር ተወያዩ። ስለዚህ ጉዳይም ለተማሪዎቻችሁ ገለጻ አድርጉላቸው። ስለ ያዕቆብ ኃጢአት ግን አይደለም።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት ሁለትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ከአባቱ ሞት በኋላ ኤሳው ያዕቆብን ስለመግደል ያስብ ነበር። ርብቃም የኤሳው ቁጣ እስኪበርድ ድረስ ያዕቆብ ወደ አጎቱ ላባን እንዲሄድና በዚያ እንዲቆይ አሰበች።<br>2. ይስሐቅ ያዕቆብን ባረከው። ያዕቆብም ወደ ፓዳን አራም ተጓዘ።<br>3. ያዕቆብ ሌሊት አረፈ። ሕልምንም አየ። ወደ ሰማይ የሚደርስ መሰላል አየ። እግዚአብሔርም ተናገረው። ዘሩ ስለሚወርሰው ምድርም የተስፋ ቃል ሰጠው። በጉዞም ከእርሱ ጋር እንደሚሆን አረጋገጠለት።<br>4. ያዕቆብም ከእንቅልፉ ነቃ። ያን ቦታም ቤቴል ብሎ ጠራው። ትርጉሙም የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው።<br>5. ያዕቆብ ለእግዚአብሔር ስዕለትን ተሳለ። እግዚአብሔር የሚጠብቀው ከሆነ እግዚአብሔርን አምላኩ እንደሚያደርግ።<br>6. እግዚአብሔር ለያዕቆብ ስላለው ፍቅር ተወያዩ። ስለዚህ ጉዳይም ለተማሪዎቻችሁ ገለጻ አድርጉላቸው። ስለያዕቆብ ኃጢአት ግን አይደለም።<br>7. እግዚአብሔር በሕይወታችን ሲሰራ ስለሚሆነው ድንቅ ነገር ተወያዩ። ስለዚህ ጉዳይም ለተማሪዎቻችሁ ገለጻ አድርጉላቸው።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሁለትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | በትናንሽ ቡድኖች ሆናችሁ ስሩ። እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር እንደነበረ እርግጠኛ የሆናችሁበትን የአንድ ቦተ ስም ጥቀሱ። ለዚህም "እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነበረ።" የሚል ርዕስ ስጡት። **ዕብራውያን 13:5** ውስጥ ያለው ሀሳብ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ያለውን ጥቅም አስቡበት። | እግዚአብሔር በሕልም ተናግሯችሁ ያውቃልን? መንፈሳዊ ትርጉም ያለው ሕልም አይታችሁ ታውቃላችሁ? ምን አይነት ትርጉም ነበረው ትላላችሁ? በሕይወታችሁ እንዴት ጠቀማችሁ? እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ሰዎችን የሚናገርባቸውን መንገዶች ጥቀሱ። በተማሪዎች የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ተዛማጅነት ያላቸውና እግዚአብሔር ሊሰጣቸው የሚችላቸው የተስፋ ቃላት ምንድናቸው? |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. ኃጢአትን የሰራችሁበትና ነገር ግን እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር የነበረበትን ወይንም ጀርባውን ያላዞረበትን እንደውም ከዚህ በተቃራኒው እናንተን የባረከበትን ጊዜ ታስታውሳላችሁ?<br>2. እንዲህ አይነቱ ልምምድ በውስጣችሁ ምን አይነት ስሜት ይፈጥራል?<br>3. እግዚአብሔር እንዴት እንዲናገራችሁ ትጠብቃላችሁ? | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. ስለመንፈሳዊ ህልሞች ጥናት አካሂዱ። እግዚአብሔርም በእንዲህ አይነት ሕልሞች እንዲናገራችሁ ዝግጁዎች ሁኑ።<br><br>2. እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰጣቸውን አራት ቃል ኪዳኖች ፈልጉ። እነኝህን ይዛችሁ ጸልዩ። |

| | ሀ7 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 – የያዕቆብ ሕይወት<br>ርዕስ – የያዕቆብ ቅሬታዎች | ሀ7 – ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – የያዕቆብ ሕይወት<br>ርዕስ – የያዕቆብ ቅሬታዎች |
|---|---|---|
| | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ***ዘፍጥረት 29: 1-30***<br><br>ቁልፍ ጥቅስ: *ገላትያ 6: 7*<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>1. ሕይወት መዘራትና ማጨድ ነው።<br>2. ሕይወት ሁልጊዜ ቀላል እንደሆነ የሚናገሩ የተስፋ ቃላት የሉም። | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ***ዘፍጥረት 29: 1-30 እና 31: 1-21***<br><br>ቁልፍ ጥቅስ: *ገላትያ 6: 7*<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>1. ሕይወት መዘራትና ማጨድ ነው።<br>2. እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር ሁሉ ለይስሙላ አይደለም።<br>3. ሌሎች ለእኛ እንዲያደርጉልን የምንሻውን እኛም ልናደርግላቸው ይገባናል። |
| መግቢያ | በእርሻና በአትክልት ስፍራ ስላለ የመዘራትና የማጨድ ስራ ተነጋገሩ። ማንኛውም የተዘራ ዘር የሚያፈራው ያንኑ አይነት ዘር እንደሆነ ግለጹላቸው። መልካምም ይሁን ክፉ የሆነ ማንኛውም ባሕርያችን የሚያስከትለው ነገር እንዳለ ተነጋገሩ። የዘራነውን እናጭዳለን!<br>መጥፎ ባሕርይ አሳይተው ለዚህ መጥፎ ባሕርያቸው ደግሞ የሚገባቸውን ያጨዱ ዘመናዊ ሰዎችን አስቡ። | በእርሻና በአትክልት ስፍራ ስላለ የመዘራትና የማጨድ ስራ ተነጋገሩ። ማንኛውም የተዘራ ዘር የሚያፈራው ያንኑ አይነት ዘር እንደሆነ ግለፁላቸው። መልካምም ይሁን ክፉ የሆነ ማንኛውም ባሕርያችን የሚያስከትለው ነገር እንዳለ ተነጋገሩ።<br>ጋዜጦችን ወይንም ደግሞ መፅሔቶችን ፈልጋችሁ አንብቡ። የመዘራትና የማጨድ ምሳሌ ሊሆኑላችሁ የሚችሉ ነገሮች ፈልጉ። ከዚያም በእነኝህ ምሳሌዎች ውስጥ ያሉ ምስሎችን እየቆራረጣችሁ ካወጣችሁ ከአጠገባቸው አብረዋቸው ሊሄዱ የሚችሉ ቃላትን እየጻፋችሁ ኮላዥ አዘጋጁ። |
| ማጠናቀቅ | የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br><br>ውይይትና ገለጻ<br>1. ያዕቆብ ወደ ካራን ምድር ደረሰ። በዚያም በጎቻቸውን ውኃ የሚያጠጡ እርኞችን አገኘ።<br>2. የአጎቱ የላባን ልጅ ራሄልም እንዲሁ በጎቿን ውኃ ልታጠጣ ወደ ጉድጓዱ መጣች። ያዕቆብም ረዳት። እርሷም የያዕቆብን መምጣት ለላባን ስትነገርው አቀባበል አደረገለት።<br>3. ያዕቆብ ለላባን መስራት ጀመረ። ሰባት ዓመት የሚያገለግለው ከሆነ በፍቅር የወደቀላትን ልጁን ራሄልን እንደሚደርለት ቃል ገባለት።<br>4. ከሰርጉ ስነስርአት በኋላ ያዕቆብ መታለሉ ገባው። ያገባው ራሄልን ሳይሆን እህቷን ልያን ነበር።<br>5. ራሄልን ሚስቱ አድርጎ ቢወስዳትም ለሌላ ሰባት ተጨማሪ አመታት ላባንን ማገልገል ነበረበት።<br>6. *ያዕቆብ ከዓመታት በፊት የፈጸማቸውን የማጭበርበር ተግባራት አሁን እንዴት እያጨደ እንደሆነ ተወያዩበት።*<br>7. *ሰዎች ቅሬታን የሚፈጥሩባቸውን ጉዳዮች እንዴት እንደሚያስተናግዷቸው ተወያዩበት።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>ትምህርት ሶስትን አጠናቁ። | የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br><br>ውይይትና ገለጻ<br>1. ያዕቆብ ወደ ካራን ምድር ደረሰ። በዚያም በጎቻቸውን ውኃ የሚያጠጡ እርኞችን አገኘ።<br>2. የአጎቱ የላባን ልጅ ራሄልም እንዲሁ በጎቿን ውኃ ልታጠጣ ወደ ጉድጓዱ መጣች። ያዕቆብም ረዳት። እርሷም የያዕቆብን መምጣት ለላባን ስትነገርው አቀባበል አደረገለት።<br>3. ያዕቆብ ለላባን መስራት ጀመረ። ሰባት ዓመት የሚያገለግለው ከሆነ በፍቅር የወደቀላትን ልጁን ራሄልን እንደሚደርለት ቃል ገባለት።<br>4. ከሰርጉ ስነስርአት በኋላ ያዕቆብ መታለሉ ገባው። ያገባው ራሄልን ሳይሆን እህቷን ልያን ነበር።<br>5. ራሄልን ሚስቱ አድርጎ ቢወስዳትም ለሌላ ሰባት ተጨማሪ አመታት ላባንን ማገልገል ነበረበት።<br>6. *ያዕቆብ ከዓመታት በፊት የፈጸማቸውን የማጭበርበር ተግባራት አሁን እንዴት እያጨደ እንደሆነ ተወያዩበት።*<br>7. በኋላም እግዚአብሔር ያዕቆብን ወደ ተወለደበት ምድር እንዲመለስ ይናገረዋል። እግዚአብሔር ባረከው። በብዙ እንስሳትና በትልቅ ቤተሰብ ባረከው። እንደሚሄድ ለላባን አልነገረውም። ነገር ግን ላባን በሰፈር ባልነበረበት ወቅት ሸሽቶ ሄደ።<br>የያዕቆብን ብዙ ውድቀቶች አስቡ። እግዚብሔር ከፍፁምነት በጣም በራቁ ሰዎች ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር እንደሚሰራ ተወያዩበት።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>ጥናት ሶስትን አጠናቁ። |
| ክለሳ | ከላይ በተራ ቁጥር 7 ካሉት ምሳሌዎች ውስጥ አንዱን ምረጡ። ከዚያም የክፍሉ ተማሪዎች ሊያዩ በሚችሉበት በአንድ ትልቅ ቻርት ላይ ጻፉ። | በሰዎች ሕይወት የመዘራትና የማጨድ ምሳሌዎች ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን አስቡ። በመጀመሪያ በአሉታዊ መንገድ ከዚያም በአዎንታዊ መንገድ። ለእያንዳንዳቸው ሁለት ምሳሌዎችን ለማቅረብ ሞክሩ። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. ቅሬታ ያስተናገዳችሁበት የመጨረሻ ጊዜ መቼ ነበር?<br>2. ይህን ቅሬታ በተመለከተ ምን አደረጋችሁ?<br>3. ይህን ቅሬታችሁን በተመለከተ ከዚህ የተሻለ ልታደርጉ የምትችሉት ነገር ነበር?<br>4. በሁለት ረድፎች የተጻፉ ሶስት የመዘራትና የማጨድ ምሳሌዎችን መዘርዘር ትችላላችሁ? | ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?<br>1. አጭበርብሮ የኖረ በኋላም የተጭበረበረ አጭበርባሪ ሰው ታውቃላችሁ?<br>2. የሰዎች መጥፎ ባሕርይ መልሶ ራሳቸውን ሲያጠቃ አይታችሁ ታውቃላችሁ? መጥቀስስ ትችላላችሁ? |

| | ሀ7– ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 – የያዕቆብ ሕይወት<br>ርዕስ – ግኙቱ | ሀ7– ደረጃ 4<br>ጥናት 4 –የያዕቆብ ሕይወት<br>ርዕስ – ግኙቱ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ዘፍጥረት32 : 1-21 እና ዘፍጥረት33: 1-11*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** *1 ዮሐንስ 1: 9*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ልክ በያዕቆብ ሕይወት እንደሆነው ሰዎች እጅግ በጣም ከፉ ነገር ቢያደርጉብንም እንኳን በእግዚአብሔር እርዳታ ይቅር ልንላቸው እንችላለን።<br><br>2. በኃጢአታችን ብንናዘዝና እግዚአብሔርን ይቅርታ ብንለምነው እግዚአብሔር ሁልጊዜም ይቅር ይለናል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ዘፍጥረት32: 1-32 እና ዘፍጥረት33: 1-17*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** *1 ዮሐንስ 1: 9*<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>1. ያዕቆብ በሕይወቱ ትልቅ ቀውስ በተፈጠረበት ጊዜ ላይ ይገኛል። ታዲያ በዚህን ጊዜ ከምንም ነገር በላይ የሚያስፈልገው ለረዥም ጊዜ ከተለየው ወንድሙ ጋር መገናኘት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት ነበር።<br>2. ምንም እንኳን ያዕቆብ ትልቅ ሰው ቢሆንም አሁንም እግዚአብሔር በያዕቆብ ሕይወት አዲስ እቅድ አለው። |
| *መግቢያ* | *ያዕቆብ እግዚአብሔርን ታዞ ወደ ተወለደበት ምድር እየተመለሰ እንደሆነ ተማሪዎቻችሁን አስታውሷቸው። ነገር ግን ከረዥም አመታት በፊት ሊገድለው ይፈልገው ከነበረው ከወንድሙ ኤሳው ጋር የመገናኘቱ ጉዳይ እጅግ በጣም አሳስቦታል። ኤሳው ምህረት ሊያደርግለት ዝግጁ እንደሆነ አስቡ። እስቲ ሰዎቸን ይቅር ስትሏቸውና ሰዎችን ይቅር ማለት ሲያቅታችሁ ሊገጥሟችሁ ስለሚችሉ ነገሮች ተነጋገሩ።* | አንድ ልዩ የሆነ ሰው ጋር ስለመገናኘት አውሩ። ለዚህ ግንኙነት ምን አይነት ዝግጅት እንደምታደርጉ አስቡ። ለዓመታት ከእግዚአብሔር ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ያልነበረው ያዕቆብ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኘ። ያዕቆብ አሁን የድሮው ያዕቆብ አይደለም። ከወንድሙ ከኤሳው ጋር ለመገናኘትም ከእግዚአብሔር ዘንድ እርዳታን ተቀበለ። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ከብዙ አመታት በኋላ ያዕቆብ ወደ ተወለደበት ምድር ለመመለስ የፈራባቸውን ምክንያቶች ተነጋገሩባቸው።<br>2. የያዕቆብ ፍርሃት የጨመረው ኤሳው አራት መቶ ሰዎችን አስከትሎ እርሱን ሊያገኘው እየመጣ መሆኑን ሲረዳ ነበር።<br>3. ያዕቆብ ሶስት ነገሮችን አደረገ። 1) ቢያንስ አንደኛው ክፍል ከኤሳው ጥቃት ሊተርፍ እንደሚችል አስቦ ቤተ ሰቡን በሁለት ክፍል ከፈለው። *(32: 7-8),* 2) ጸለየ። *(32: 9-12),* 3) ለኤሳው ስጦታ ላከለት። *(32: 13-16)*<br>4. በዚያ ለሊት ያዕቆብ እግዚአብሔርን እንግዳ በሆነ መንገድ ተገናኘ። ከእግዚአብሔር ዘንድም በረከትን ለመነ። *(32: 22-31)*<br>5. የያዕቆብ ፍርሃት መሰረት የለሽ ፍርሃት ነበር። ኤሳው አቀፈው። በደሉንም ይቅር ያለው ይመስላል። ያዕቆብም ኤሳውን ከቤተ ሰቡ አባላት ጋር አስተዋወቀው። ስጦታውን እንዲቀበል የግድ አለው።<br>6. እስካሁን ወደ አባቱ አልተመለሰም። ወዲያው ባለመመለሱም ኤሳውን አሁንም አታለለው።<br>7. *እግዚአብሔርን ለምን እንደተጠራጠረና የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል አምኖ ሊቀበለው እንዳልቻለ ተነጋገሩበት።*<br>8. *ፍርሃቶቻችሁን አጋሯቸው። እንዲሁም አብዛኞቹ ስለእነርሱ እያሰብን ብዙ ጊዜ የምንወስድባቸው አስፈሪ ነገሮች እንደፈራናቸው እንደማይሆኑ ግለፁላቸው።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምርት አራትን አጠናቁ።** | የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br><br>ውይይትና ገለጻ<br>1. ከብዙ አመታት በኋላ ያዕቆብ ወደ ተወለደበት ምድር ለመመለስ የፈራባቸውን ምክንያቶች ተነጋገሩባቸው።<br>2. ከብዙ አመታት በኋላ ያዕቆብ ወደ ተወለደበት ምድር ለመመለስ የፈራባቸውን ምክንያቶች ተነጋገሩባቸው።<br>3. ያዕቆብ ሶስት ነገሮችን አደረገ። 1) ቢያንስ አንደኛው ክፍል ከኤሳው ጥቃት ሊተርፍ እንደሚችል አስቦ ቤተ ሰቡን በሁለት ክፍል ከፈለው። *(32: 7-8),* 2) ጸለየ። *(32: 9-12),* 3) ለኤሳው ስጦታ ላከለት። *(32: 13-16)*<br>4. በዚያ ለሊት ያዕቆብ እግዚአብሔርን እንግዳ በሆነ መንገድ ተገናኘ። ከእግዚአብሔር ዘንድም በረከተን ለመነ። *(32: 22-31)*<br>5. የያዕቆብ ፍርሃት መሰረት የለሽ ፍርሃት ነበር። ኤሳው አቀፈው። በደሉንም ይቅር ያለው ይመስላል። ያዕቆብም ኤሳውን ከቤተ ሰቡ አባላት ጋር አስተዋወቀው። ስጦታውን እንዲቀበል የግድ አለው።<br>6. እስካሁን ወደ አባቱ አልተመለሰም። ወዲያው ባለመመለሱም ኤሳውን አሁንም አታለለው።<br>7. *እግዚአብሔርን ለምን እንደተጠራጠረና የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል አምኖ ሊቀበለው እንዳልቻለ ተነጋገሩበት።*<br>8. *የሌሎችን በደል ይቅር ስላሉ ትክክለኛ ሰዎች ታሪክ ተወያዩ።*<br>9. *የበደሉንን ይቅር ማለት ሳንችል ስንቀር በራሳችንና በሌሎች ላይ ልናደርስ ስለምንችለው ጉዳት አስቡ።*<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>ጥናት አራትን አጠናቁ። |
| ክለሳ | ከላይ ያለውን ክፍል መልሳችሁ በማየት ለእግዚአብሔር ደብዳቤ ለመጻፍ ተዘጋጁ። በዚህ ደብዳቤ ተማሪዎቻችሁ በእግዚአብሔር ፊት ሊናዘዙት ስለሚገባ ነገር፣ መለመን ስለሚፈልጉት ነገር፣ እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑበት ስለሚገባቸው ነገር ጠይቋቸው። | ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት ማለት ምን ማለት እንደሆነ አስቡ።<br>ሀ/ መቼ ሊሆን ይችላል?<br>ለ/ እንዴት ሊሆን ይችላል?<br>ሐ/ ለምን ሊሆን ይችላል?<br>ተማሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር በግል ተገናኝተው ያውቁ እንደሆነ ጠይቋቸው። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. ከሕይወታችን ጋር ሊዛመድ የሚችለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምን ልንማር እንችላለን?<br>2. በቅርብ ጊዜ ይቅርታን የተቀበለ የአንድ ሰው ምሳሌ ስጡ።<br>3. እግዚአብሔር ሌሎች ሰዎች ይቅርታ ማለት እንድንችል እንዲረዳን ልንጠይቀው እንችላለን? | ***ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?***<br>1. ተማሪዎቻችሁን በቅርብ ጊዜ ይቅርታ ሊያደርግላቸው ስላልቻለ ወይንም ይቅር ስላላቸው አንድ ሰው እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው።<br>2. ምን ተሰማቸው?<br>3. እነርሱስ ይቅር ሊሉት የሚገባ ሰው አለ? |

| | ሀ8– ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 – ክርስቲያን መሆን<br>ርዕስ – ጸሎት ምንድነው? | ሀ8 – ደረጃ 4<br>ጥናት 1 – ክርስቲያን መሆን<br>ርዕስ – ስለጸሎት መማር |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***መዝሙር 5: 1-8***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***መዝሙር 5: 2***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. እግዚአብሔር ልዩ ስለሆነ ጸሎትም እንዲሁ ልዩ ነው።<br>2. ጸሎት ለእግዚአብሔር መናገርና እርሱን መስማት ማለት ነው።<br>3. አንዳንዴ ጸሎታችን አይመለስም። ለዚህ ደግሞ ምክንያቶች አሉት። | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ***ሉቃስ 11: 1-10 እና ማቴዎስ 6: 5-15***<br><br>ቁልፍ ጥቅስ: *ሉቃስ 11: 9*<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>1. ጸሎት ትልቅ መብት እንደሆነ መረዳት አለብን።<br>2. ያለማቋረጥ መጸለይ አለብን።<br>3. በግል ጸሎታችን ትኩረታችንን በራሳችን ላይ ማድረግ የለብንም። |
| መግቢያ | ከእናንተ ርቀው ከሚኖሩ ጓደኞቻችሁና ከቤተ ሰቦቻችሁ ጋር ለመገናኘት ስትጥሩ ስለሚገጥማችሁ ችግር አስቡ። ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት ስለመቻላችን አስደናቂ እውነት አስቡ።<br>ተማሪዎቻችሁ ይጸልዩ እንደሆነ ጠይቋቸው። ከጸለዩ ለምን? ካልጸለዩ ለምን? | ከእናንተ ርቀው ከሚኖሩ ጓደኞቻችሁና ከቤተ ሰቦቻችሁ ጋር ለመገናኘት ስትጥሩ ስለሚገጥማችሁ ችግር አስቡ። ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ መገናኘት ስለመቻላችን አስደናቂ እውነት አስቡ።<br>ልንጸልይባቸው ስለሚገቡ ነገሮች አስቡ። ተማሪዎች ስለተመለሱ ጸሎቶቻቸው ያስታውሱ እንደሆነ ጠይቋቸው። ለተመለሰላቸው ጸሎት ምላሻቸው ምን ነበር? |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ስንጸልይ ከማን ጋር እንደምንነጋር አስቡ። ዳዊት በመዝሙሩ ስለተጠቀመባቸው አንዳንድ ርዕሶች አስቡ።<br>2. ዳዊት በየትኛው በምን ሰዓት እንደጸለየ አስቡ። እኛም መቼ መጸለይ እንዳለብን ተወያዩበት።<br>3. ከመዝሙሩ እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንዳይሰማ ሊከለክሉ የሚችሉ ነገሮች ምን እንደሆኑ ተናገሩ።<br>4. እንዲሁም ከዚህ መዝሙር የምንማረውና እኛን ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት ለምናደርገው ግንኙነት የሚረዳን ምን ትምህርት እንማራለን?<br>5. በቁጥር 2 ላይ ዳዊት እግዚአብሔርን ንጉሴና አምላኬ ብሎ መጥራቱ በእርሱና በአግዚአብሔር መካከል ልዩ ሕብረት እንዳለ ያሳያል። እንዲህ አይነት የተለያ ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት ሊኖረን ይችላል?<br>6. *ጸሎት እንዴት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ተወያዩ። ገለጻም አድርጉላቸው። ለምሳሌ ሕይወት ያለጸሎት ምን እንደሚመስል ልታስረዷቸው ትችላላችሁ።*<br>7. ስለምን ጉዳይ መጸለይ እንችላለን?<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አንድን አጠናቁ።** | የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br><br>ውይይትና ገለጻ<br>1. በአንድ አጋጣሚ ኢየሱስ ይጸልይ ነበር። ደቀ መዛሙርቱም እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው እንዲያስተምራቸው ጠየቁት።<br>2. ስንጸልይ ከማን ጋር ነው የምንነጋገረው? እንዲሁም ኢየሱስ ስለተጠቀመበት ርዕስ አስቡ።<br>3. ኢየሱስ የናሙና ጸሎቱን የጀመረው እግዚአብሔርን በማመስገን ነበር። የትኛው የጸሎታችን ክፍል ነው ምስጋና ሊኖረው የሚገባ?<br>4. በዚህ ናሙና ጸሎት ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ስላቀረባቸው ሶስት ልመናዎች አስቡ።<br>5. ከዚያመ ኢየሱስ ስለተናገረው ምሳሌ አንብቡ። ***(ሉቃስ 11: 5-10)*** እንዲሁም ያለማቋረጥ ጸንተን መጸለይ እንዳለብን ኢየሱስ ያስተማረውን ትምህርት እዩት።<br>6. **በማቴዎስ 6፡5-15** ኢየሱስ ስለጸሎት ያስተማረውን ትምህርት አስቡ።<br>7. *ለምን ችግሮች ሲመጡ አብዝተን እንደምንጸልይ አስቡ።*<br>8. *አንዳንዴ መጸለይ ከባድ የሚሆንብን ለምን እንደሆነ አስቡ።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>ጥናት አንድን አጠናቁ። |
| ክለሳ | እንድንጸልይላቸው የሚሹ ሰዎች ወይንም እንድንጸልይባቸው የሚፈልጉ ጉዳዮች አሉ? ለምን ያህል ጊዜ ነው መጸለይ ያለብን?<br>ስለ አንድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለጸለየ ሰው አስቡ። ከዚህ ሰው የጸሎት ሕይወት ምን እንማራለን? | በጥናት አንድ ከተጠቀሱት ባሕርያት አምስቱን በአጭር በአጭሩ አውሩ። ተማሪዎቻችሁንም እነኝህን ባሕርያት በሙሉ የያዘ ጸሎት በጋራ እንዲጸልዩ ጠይቋቸው። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>በጸሎት ጊዜ ብዙ ማድመጥ ወይንስ ብዙ መናገር ነው የሚገባን? ምናልባትም እግዚአብሔ የሚለንን ለመስማት መዘጋጀት ይገባን ይሆናል። | ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?<br>ሊጸለይባቸው ስለሚገቡ የግል፣ የቤተ ሰብ፣ የማህበረሰብ፣ የአገርና አለም አቀፍ ጉዳዮች አስቡ። ለተመለሱ ጸሎቶች ምስጋና ማቅረባችሁን አትርሱ። |

| | ሀ8– ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 – ክርስቲያን መሆን<br>ርዕስ – እግዚአብሔር ጸሎታችንን ይሰማልን? | ሀ8 – ደረጃ 4<br>ጥናት 2 – ክርስቲያን መሆን<br>ርዕስ – ስለመጽሐፍ ቅዱስ እንማር። |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***ሉቃስ 18: 9 -14***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ያዕቆብ 4: 6***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው  የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመጸለይ መሄድ አያስፈልገንም። የትም ቦታ ሆነን በየትኛውም ጊዜ መጸለይ እንችላለን።<br>2. እግዚአብሔ ስንጸልይ እውነተኞችና ትሁታን መሆን አለብን። | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ***ሐዋርያት ስራ 17: 10-14 እና 2 ጢሞቴዎስ 3: 14-17***<br><br>ቁልፍ ጥቅስ: *መዝሙር 119: 105*<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው  የሚከተሉትን ነው።<br>1. መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ በጣም ጠቃሚ ነው።<br>2. መጽሐፍ ቅዱስን እናምነዋለን። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ነውና! |
| *መግቢያ* | በትህምርት 1 ስለ ጸሎት የተማርነውን አሁን ከልሱ። መጽሐፍ ቅዱስ በ**ምሳሌ 16፡18** “ትዕቢት ጥፋትን፥ ኵሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል።” ይህ ምን ማለት እንደሆነ አስቡ። ከእውነተኛ የሕይወት ታሪክ ወይንም ደግሞ ከልብ ወለድ ታሪክ ተነስታችሁ ይህን ሐሳብ አብራሩ። | ከማንኛውም መጽሐፍ ይልቅ የሚበረከተው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በዘመናት ብዙ አገሮች መጽሐፍ ቅዱስን በሕግ ለመከልከል ወስነው ነበር። አቃጥለውታል። ቀብረውታል። ሆኖም በዚህ ሁሉ አልፎ ዛሬም አለ። ለዚህ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ኢየሱስ ሁልጊዜ መጸለይና ተስፋ መቁረጥ እንደሌለብን በቁጥር 1 ላይ ያስተምረናል። ***(ቁጥር 1)***<br>2. በትዕቢት የተሞሉና ትህትና የሌለባቸው ሰዎች ትክክለኛ የጸሎት አመለካከት የሌላቸው ሰዎች ናቸው። ***(ቁጥር 9)***<br>3. ፈሪሳዊው ሰው (ኃይማኖተኛው ሰው) ምን ያህል ጊዜ “እኔ” የሚለውን ቃል እንደተጠቀመበት ተመልከቱ።<br>4. ተማሪዎች የቀራጩን ጸሎትና ስለጸሎት ያለውን አመለካከት እንዲያብራሩ ተማሪዎቻችሁን ጠይቁ።<br>5. *እነኝህ ሁለት ሰዎች ያላቸውን የጸሎት አቀራረብ ልዩነት አወዳድሩ።*<br>6. *ከሁለቱ የትኛው ሰው እግዚአብሔርን እንዳስደሰተ አብራሩ። ለምን?*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት ሁለትን አጠናቁ።** | የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br><br>ውይይትና ገለጻ<br>1. ለክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ከሁሉም ነገር ይልቅ ዋነኛ መጽሐፍ ነው። እውነት ለመሆኑ እርግጠኛ የምንሆነው እንዴት ነው?<br>2. የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ የሚነግረን የእግዚአብሔር ቃል በሙሉ የእግዚአብሔር እስትንፋስ እንዳለበት ነው። ይህ ማለት ቅዱሳን በእግዚአብሔር ተነድተው ነው የጻፉት ማለት ነው። እግዚአብሔር አይዋሽም። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት እንደሆነ እርግጠኛ መሆን እንችላለን።<br>3. ብዙ ነገሮች የተተነበዩት በብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ ነበር። ፍጻሜ ያገኙት ግን አንዳንዴ ከብዙ ዓመታት በኋላ ነበር።  እንደምሳሌ ማንሳት የምንችለው ስለኢየሱስ ውልደት የሚናገሩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ነው።<br>4. የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን የጻፉት ወደ አርባ የሚጠጉ ሰዎች ሲሆኑ ይህም በብዙ ምዕተ ዓመታት ልዩነት ውስጠ ነው። ሆኖም ሁሉንም መጽሐፍት በመጣጣም እንዲጣመሩ የሚያደርጋቸው አንድ መካከለኛ እውነት አለ።<br>5. በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና ስብከቶችን መስማት የሰዎችን ሕይወት ይለውጣል።<br>6. መጽሐፍ ቅዱስ በጣም አስፈላጊ መሆኑ ምንም አያስገርምም። መጽሐፍ ቅዱስን የምናነብባቸው ሌሎች ምክንያቶችን አስቡ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>ጥናት ሁለትን አጠናቁ። |
| ክለሳ | በንፁሕ ወረቀት ላይ ቀራጩ ያሳያቸውን መልካም ባሕርያት በዝርዝር ጻፉ። እንዲሁም ፈሪሳዊው የታዩበትን ባሕርያት ዘርዝራችሁ ጻፉ። | ስለቁልፍ ጥቅሱ አሰላስሉ። ከዚያም ከሰማይ የሚመጣ የብርሃን ጨረር ስዕልን ሳሉ። ከበታቹም የእግዚአብሔር ብርሃን እንዲበራባቸው ጉዳዮቻችሁን ንደፏቸው ወይንም ጻፏቸው። ለምሳሌ ያህል በጣም አንገብጋቢ የሆነ ውሳኔ ሊሆን ይችላል። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. ትህትና የሚለው ቃል ምን ማነት ነው። እንዴትስ ትሁታን መሆን እንችላለን? ትህትናን ማሳየት የምንችልባቸውን ምሳሌዎች ስጡ።<br>2. ኩራት ወይንም ትዕቢት የሚው ቃል ምን ማለት ነው? በሕይወታችን ያለን የኩራት ዕቢት መጠን እንዴት መቀነስ እንችላለን? ትዕቢተኝነትን/ኩራትን ማሳየት የምንችልባቸውን ምሳሌዎች ጥቀሱ። | ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?<br>1. መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ የሚረዱ ተግባራዊ መንገዶች ምንድናቸው?<br>2. መጽሐፍ ቅዱስን ደጋግመን ማንበብ፣ በተሻለ መንገድ መረዳትና በሕይወታችን ለመተርጎም እንድንችል እግዚአብሔርን ለምኑት። |

| | ሀ8 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 – ክርስቲያን መሆን<br>ርዕስ – እንዴት ነው መጸለይ ያለብን? | ሀ8 – ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – ክርስቲያን መሆን<br>ርዕስ – ለእግዚአብሔር መኖር |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ማቴዎስ 6: 5-15*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *ማቴዎስ 6: 8*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. በመደበኛነት መጸለይ አለብን እንጂ ነገሮች ሲበለሻሹ ብቻ ልንጸልይ አይገባም።<br>2. ጸሎት ረዥምና የቅንጦት መሆን የለበትም።<br>3. የጌታ ጸሎት ጸሎታችን ምን መምሰል እንደላበት የሚረዳን የጸሎት ናሙና ነው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ዮሐንስ 15: 1-17 እና ገላትያ 5: 22-23*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *ዮሐንስ 15: 5*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ክርስቲያኖች በየእለቱ ኢየሱስን እየመሰሉ መሄድ አለባቸው።<br>2. በወይኑ ግንድና በቅርንጫፉ ምሳሌ እንደምናየው ወደ እርሱ መቀርብ ለዚህ ዋነኛ ምስጢሩ ነው።<br>3. ክርስቲያኖች በየቀኑ በእግዚአብሔር እጅ ሊገረዙና የበለጠ መልካም ፍሬ ማፍራት መቻል አለባቸው። |
| መግቢያ | 1. ትምህርት አንድና ሁለትን እንዲሁም ስለጸሎት እስካሁን ድረስ የተማርነውን ትምህረት ከልሱ። በመደበኛነት መጸለይ ለብዙዎች ችግር የሆነበትን ምክንያት አስረዱ።<br>2. ጮክ ብሎ መጸለይ ትኩረታችንን ለመሰብሰብ እንዴት ይጠቅመናል?<br>3. ጸሎታችንን በጽሁፍ ማድረግ ትክክለኛ የጸሎት ቃላትን ለመምረጥ እንዴት ይጠቅመናል? | 1. ፍሬያማ ስለሆኑና የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ስለሚታዩባቸው ክርስቲያኖች አስቡ። እንዴትም በሕይወታቸው ፍሬያማ ሊሆኑ እንዴት እንደቻሉ አስቡ።<br>2. ልክ የወይን ሰራተኛው ወይኑን እንዲያፈራ እንደሚገርዘው ሁሉ እግዚአብሔርም ከሕይወታችን የማይረቡና የኃጢአት ውጤት የሆኑ ነገሮችን ለማሰወገድ በሕይወታችን ይሰራል። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጌታ ስለጸሎት ያስተማረው በተራራው ስብከት ነበር።<br>2. ጸሎት እንዴት ነው በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ያለ የግል ጉዳይ የሆነው?<br>3. ዝም ብሎ ቃላትን መደጋገም ብቻ ጸሎት ሊሆን የማይችለው ለምንድነው?<br>4. እግዚአብሔር ሳንለምነው የሚያስፈልገንን የሚያውቅ ከሆነ ጸሎት ለምን ያስፈልጋል?<br>5. የጌታን ጸሎት ከምስጋናና ከልመና አንጻር ቅደም ተከተሉን አሰላስሉ።<br>6. ስንጸልይ እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንደሚሰማን ስንገልጽ በእግዚአብሔር ማመናችን ጥቅሙ ምን እንደሆነ አሰላስሉ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br><br>**ትምህርት ሶስትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. እግዚአብሔር አብን እንደ ወይን አትክልተኛው፣ ጌታ ኢየሱስን እንደወይኑ ግንድና ክርስቲያኖችን ደግሞ እንደወይኑ ቅርንጫፍ ግለጹት።<br>2. እግዚአብሔር በሕይወታችን ብዙ ፍሬዎች ማየትን ይሻል። ይህ ደግሞ በሚገባ የተገለጸው **በገላትያ 5፡ 22-23** ላይ ነው።<br>3. ፍሬ የሚሰጡ ዛፎች ከመገረዛቸው በፊትና በኋላ ምን እንደሚመስሉ አስቡ። ለምን ይመስላችኋል ዛፍን የመግረዝ ሂደት ብዙ ፍሬ ለማፍራት የሚያስችለው እንዴት ነው?<br>4. **ገላትያ 5፡ 19-20** ላይ የተጠቀሰውን ምንም የመንፈስ ቅዱስ ስራ የሌለበትን የስጋ ፍሬ አነጻጽሩት።<br>5. የእግዚአብሔር አላማ እንደክርስቲያኖች ልክ በሕይወቱ ሁሉም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች የታዩበትን ክርስቶስን በብዙ እንዲመስሉት ይፈልጋል።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሶስትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | ሰለ ***1ኛ ጢሞቴዎስ 2: 1*** አሰላስሉ። ስለተለያዩ የጸሎት አይነቶች ተወያዩ። በግል ልንጸልይባቸው የምንችልባቸውን ቦታዎች ጥቀሱ። ተማሪዎች የግል የጸሎት ቦታዎች እየተናገሩ እናንተ ጻፉ። | በዚህ ጥናት ውስጥ የተማርናቸውን ትምህርቶች አጠቃሉ። ቁልፍ ሀሳቡ **በዮሐንስ 15፡ 4 – 5** እንደተጠቀሰው በእርሱ መኖር ነው። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ጸሎት ሙት ሳይሆን ሕይወት ያለው የሕይወታችን ክፍል ነው። አሁን ይህ ለእናንተ ምን ማለት እንደሆነ አሰላስሉ። ስትጸልዩ እምነት እንዲኖራችሁ እግዚአብሔነርን ለምኑት። ተማሪዎች የጌታን ጸሎት ቅደም ተከተል ተጠቅመው እንዲጸልዩ አበረታቷቸው። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ተማሪዎች በጸሎት መንፈስ ሆነው **ገላትያ 5፡ 22 -23**ን እንዲያነቡ ጠይቋቸው። ከእነኚህ ፍሬዎች መካከል እግዚአብሔር በሕይወታችን እንዲዳብሩ የሚፈልጋቸውንና የእርሱን እርዳታ የሚሹባቸውን ፍሬዎች መለየት እንዲችሉ ጠይቋቸው። |

| | ሀ8– ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 – ክርስቲያን መሆን<br>ርዕስ – እግዚአብሔር ጸሎታችንን ይሰማልን? | ሀ8 – ደረጃ 4<br>ጥናት 4 – ክርስቲያን መሆን<br>ርዕስ – ለእግዚአብሔር መስጠት |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *1 ሳሙኤል 1: 1-20*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *1 ሳሙኤል 1: 20*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ጸሎቶቻችን ብዙውን ጊዜ እኛ በምንፈልገው መንገድና ፍጥነት አይመለሱም።<br>2. የእግዚአብሔር መልሶችና እቅዶቹ ሁልጊዜም ከእኛ ይሻላሉ።. | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: *ማርቆስ12: 41-44 እና ማቴዎስ 6: 1-4*<br><br>ቁልፍ ጥቅስ: *2 ቆሮንቶስ 9: 7*<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>1. ለእግዚአብሔር በልግስና መስጠት ይገባናል። ይህም የሕይወታችን ዋና ተግባር ሊሆን ይገባዋል።<br><br>2. ለእግዚአብሔር የምንስጠው ገንዘባችንን ብቻ አይደለም። |
| መግቢያ | ሀናንና የነበረችበትን ሁኔታ አስተዋውቁ።<br>የሃናን ስሜቶች ለመግለፅ በግድግዳ ላይ የሚለጠፉ ስዕሎችና ቃላትን አዘጋጁ።<br>ከጸሎት በኋላና + ከጸሎት በፊት | በትንንሽ ቡድኖች በክብ ሆናችሁ እግዚአብሔር ለእኛ ስለሚሰጠን ነገሮችና እኛ ደግሞ ለእርሱ ልንሰጠው ስለምንችላቸው ነገሮች ዝርዝር አዘጋጁ። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. በአጭር ሃናና ቤተ ሰቧ የነበረበን ሁኔታ ግለጹላቸው። ለአምልኮና ለመስዋዕት ወደ እግዚአብሔር ቤት በየአመቱ እየሄዱ ስለሚያደርጉት ጉብኝትም ግለጹላቸው።<br>2. ሃና ልጆች አልባ መሆኗና የፍናና አነጋገር ምን አይነት ስሜት ሊፈጥርባት እንደሚችል አስረዷቸው።<br>3. ስለሀና ጸሎትና እግዚአብሔር ስለገባላት ቃል ኪዳን አሰላስሉ።<br>4. ስለሀና ጸሎት የካህኑ ኤሊ ምላሽ ምን እንደነበር አስረዷቸው።<br>5. እግዚአብሔር የሀናን ጸሎት እንዴት እንደመለሰ አስረዷቸው።<br>6. ኤሊ ከጸለየላት በኋላ በውስጧ የተፈጠረውን የተለየ ስሜትና ጭንቀቷን በእግዚአብሔር ላይ እንዴት እንደጣለች አሰላስሉ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አራትን አጠናቁ።** | የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br><br>ውይይትና ገለጻ<br>1. ኢየሱስ ሰዎች በመቅደሱ ውስጥ የገንዘብ ስጦታን ለእግዚአብሔር እንዴት እንደሚሰጡ አስረዱ።<br>2. ከሌሎቹ ሰዎች ሁሉ ይልቅ የመበለቲቱ ስጦታ የበለጠው ለምን እንደሆነ ግለጹ።<br>3. ለምንድነው ጌታ ኢየሱስ በመበለቲቱ አነስተኛ ስጦታ ደስተኛ የሆነው?<br>4. ይህ አጋጣሚ ጊዜያችንን፣ ክህሎቶቻችንንና ሀብታችንን ስለመስጠት ምን ያስተምረናል?<br>5. በምስጢር እንድንሰጥ ጌታ ያስተማረን ለምንድነው?<br>6. በምስጢር ለሚሰጡ እግዚአብሔር ሰለገባላቸው ቃል ኪዳን አሰላስሉ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>ጥናት አራትን አጠናቁ። |
| ክለሳ | 1. በአንድ ነገር ላይ በጣም አዝነው ያውቁ እንደሆነ ተማሪዎቻችሁን ጠይቋቸው።<br>2. በዚያን ጊዜ ምን ማድረግ እንደነበረባቸው ጠይቋቸው።<br>3. ጭንቀቶቻቸውን በእግዚአብሔር ላይ መጣላቸው የተሻለ ስሜት በውስጣቸው ስለመፍጠር አለመፍጠሩን ተወያዩበት። | 1. ለእግዚአብሔር ልንሰጥባቸው የተለያዩ መንገዶች ተወያዩ።<br>2. በዛሬው ጥናት መሠረት በተግባር ልንገልጸው የምንችል አንድ ነገር ምረጡ።<br>3. ተማሪዎች ሲሰጡ በትክክለኛ የመስጠት መንፈስ ውስጥ ሆነው እንደሆነ ጠይቋቸው። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>እግዚአብሔር ጭንቀቶቻቸውን እንደሚወስድላቸው በማወቃቸው ጥቅም እንደሚያገኙና የተሻለ ስሜት ሊኖራቸው እንደሚችሉ ልትነግሯቸው ያሰባችኋቸውን ሰዎች አስቡ። | ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?<br>ከመስጠት ጋር የተገናኙ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ፈልጉ። ለምሳሌ **የሐዋርያት ስራ 20:35** ላይ "ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብጹዕ ነው።" ይህን መርህ ከመረዳት አኳያ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጠይቁት። |

| | ሀ9 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – አቃቤ ሕጉ | ሀ9 - ደረጃ 4<br>ጥናት 1 – ሐዋርያው ጳውሎስ<br>ርዕስ – ሕይወቱ ሲለወጥ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***የሐዋርያት ስራ 9: 1-19***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***2 ቆሮንቶስ 5: 17***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ጳውሎስ ኢየሱስን ካገኘ በኋላ ሕይወቱ ተለወጠ።<br>2. ዛሬም እግዚአብሔር ሕይወታችንን ይለውጣል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***የሐዋርያት ስራ 9: 1-30***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***2 ቆሮንቶስ 5: 17***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. እግዚአብሔር ብቻ ሕይወትን ይለውጣል።<br>2. ክርስቲያን መሆን በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል። ሆኖም እግዚአብሔር በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ጊዜያት እንኳን ሳይቀር ከክርስቲያኖች ጋር ነው። |
| መግቢያ | በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሳውልን እንደዋና ባሕርይ አስተዋውቁት። ከእስጢፋኖስ አሟሟት ጋር ያለውን ግንኙነት ግለፁ። (*የሐዋርያት ስራ 6: 58)*<br>በሕይወት መለወጥን አስመልክቶ አስመልክቶ ከትል ወደ ቢራቢሮነት የሚደረግ የለውጥ ሒደትን ተጠቀሙ። | በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሳውልን እንደዋና ባሕርይ አስተዋውቁት። ከእስጢፋኖስ አሟሟት ጋር ያለውን ግንኙነት ግለጹ። (*የሐዋርያት ስራ 6: 58)*<br>በሕይወት መለወጥን አስመልክቶ አስመልክቶ ከትል ወደ ቢራቢሮነት የሚደረግ የለውጥ ሒደትን ተጠቀሙ። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. በዚህ ታሪክ ለረዥም ጊዜ ጳውሎስ ሳውል ተብሎ ይጠራ እንደነበረ ግለጹ።<br>2. ወደ ደማስቆስ የተጓዘበትን ዝርዝር ምክንያት ስጡ።<br>3. ምን እንደሆነ በጥንቃቄ አጥኑ። እንዲሁም ሳውል ጌታ ኢየሱስን ሲገናኝ ምን እንደተባለ በጥንቃቄ አጥኑ። ጳውሎስ የሰጣቸው ምስክርነቶች ወደ በስተኋላ ጠቃሚዎች ይሆናሉ። ***(የሐዋርያት ስራ 22: 1-13 እና 26: 9-18)***<br>4. ወደ ደማስቆስ ከተወሰደ በኋላ ምን እንደሆነና የተሰጠው ትዕዛዝ ምን እንደነበረ አስረዱ።<br>5. የመለወጥ ትርጉሙ ምን እንደሆነ አሰላስሉ። መለወጥ እግዚአብሔር በጸጋው በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚሰራው ስራ ነው። በዚህም በክርስቶስ ያሉ ሰዎችን አዲስ ያደርጋቸዋል። ይህን እንደገና ከመወለድ ጋር አገናኙት። (***ዮሐንስ 3: 3***).<br>6. ኢየሱስን ከተገናኙ በኋላ ጳውሎስ እንዴት እንደተለወጠ አስረዱ።<br>7. ይህ መልዕክት ከክርስትና እምነት ጋር ተያይዞ በጣም አስፈላጊነቱን አፅንኦት ሰጥታችሁ ተነጋገሩ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አንድን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. በዚህ ታሪክ ለረዥም ጊዜ ጳውሎስ ሳውል ተብሎ ይጠራ እንደነበረ ግለጹ።<br>2. ወደ ደማስቆስ የተጓዘበትን ዝርዝር ምክንያት ስጡ።<br>3. ምን እንደሆነ በጥንቃቄ አጥኑ። እንዲሁም ሳውል ጌታ ኢየሱስን ሲገናኝ ምን እንደተባለ በጥንቃቄ አጥኑ። ጳውሎስ የሰጣቸው ምስክርነቶች ወደ በስተኋላ ጠቃሚዎች ይሆናሉ። ***(የሐዋርያት ስራ 22: 1-13 እና 26: 9-18)***<br>4. ወደ ደማስቆስ ከተወሰደ በኋላ ምን እንደሆነና የተሰጠው ትዕዛዝ ምን እንደነበረ አስረዱ።<br>5. የመለወጥ ትርጉሙ ምን እንደሆነ አሰላስሉ። መለወጥ እግዚአብሔር በጸጋው በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚሰራው ስራ ነው። በዚህም በክርስቶስ ያሉ ሰዎችን አዲስ ያደርጋቸዋል። ይህን እንደገና ከመወለድ ጋር አገናኙት። (***ዮሐንስ 3: 3***)<br>6. ኢየሱስን ከተገናኙ በኋላ ጳውሎስ እንዴት እንደተለወጠ አስረዱ።<br>7. ጳውሎስ ተለወጠ ስንል 'ኃይማኖተኛ ' ተደረገ ማለታችን አይደለም። ኃይማኖተኛ የነበረው ከመለወጡ በፊት እንደነበር አስታውሱ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አንድን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | የሳውል ሕይወት ከመለወጡና ከተለወጠ በኋላ የሚያሳይ የግድግዳ ስዕል አዘጋጁ። | ከመማር አላማዎች አንደኛውን ምረጡ። ከዚያም ይህ በሕይወታችሁ እንዴት ለውጥ ማምጣት እንደሚችል የሚገልፅ ጸሎት ጻፉ። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | ***ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?***<br>1. *ተማሪዎች ስላሉበት ሁኔታ እንዲናገሩ አድርጓቸው።*<br>2. ከአናንያስ ስለመታዘዝ ምን ልንማር እንችላለን? ስለመታዘዝ ልንማራቸው በምንችላቸው ነገሮች ላይ ተመስርታችሁ ልታደርጓቸው የሚገቡ ነገሮችን ዝርዝር አዘጋጁ።<br>3. ክርስቲያኖች ለአዲስ ክርስቲያን መፅናናትና መበረታታት ማድረግ ስለሚችሏቸው ነገሮች አሰላስሉ። | ***ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?***<br>1. *ተማሪዎች ስላሉበት ሁኔታ እንዲናገሩ አድርጓቸው።*<br>2. በስደት ላይ ላሉ ክርስቲያኖች ጸልዩ።<br>3. ***1 ጢሞቴዎስ 1: 12-16*** አንብቡ። ካልተለወጡ ጓደኞቻችሁ ቁጥር 15ን ለመነጋገር አስቡ። |

| | ሀ9 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 – የጳውሎስ ጉዞዎች<br>ርዕስ – ችግሮች | ሀ9 - ደረጃ 4<br>ጥናት 2 – ሐዋርያው ጳውሎች<br>ርዕስ – ጉዞዎቹ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 9: 19-30*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *ሮሜ 1: 16*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የወንጌልን መልዕክት ስለማይረዱ ክርስቲያን መሆን ከባድ ነገር ነው።<br>2. አዳዲስ ክርስቲያኖችን ማበርታት በጣም ጠቃሚ ነው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 11: 19-26; 13: 1-12*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *የሐዋርያት ስራ 13: 12*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. መለወጥ በክርስቶስ ያለ አዲስ ሕይወት ጅማሬ ነው።<br>2. አዳዲስ ክርስቲያኖች የክርስትናን ሕይወት እንዲረዱት ማስተማር እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። |
| መግቢያ | ማበረታታት ለምን አሰፈላጊ እንደሆነ ተወያዩበት። ተማሪዎች በሕይወታቸው የተበረታቱበትን ጊዜ እንዲያስቡ ጠይቋቸው። ይህ ለእነርሱ እንዴት ጠቃሚ ነበር? | ምግብ ለአካላዊ እድገታችን ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ተወያዩበት። መንፈሳዊ እድገት ለክርስቲያኖች አስፈላጊነቱን ተወያዩበት። መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ከፍታችሁ ከተማሪዎች መካከል አንደኛው **2ኛ ጴጥሮስ 2፡2 እና 2ኛ ጴጥሮስ 3፡18**ን እንዲያነብ አደርጉ። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. በደማስቆስ ጳውሎስ መስበክ ሲጀመር ምን እንደሆነ አስረዱ። መልእክቱስ ምን ነበር?<br>2. አይሁዳውያን ለምን እንደጠጡትና እርሱም እንዴት እንዳመለጠ ግለጹ።<br>3. ጳውሎስ የገጠሙትን ችግሮችና ሰዎች ለምን ወንጌልን እንደተቃወሙ ተወያዩባቸው። ለምንድነው ጳውሎስ በወንጌል ያላፍረው? (ቁጥር 2ን ተመልከቱ)<br>4. ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ የገጠሙትን ችግሮች አስረዱ።<br>5. በርናባስ ለሳውል ምን ያህል ጠቃሚ እንደነበረ ተነጋገሩበት። እንዲሁም በክርስቲያን ሕይወት ማበረታቻ ማድረግ ጠቀሜታው ምን እንደሆነ ተነጋገሩበት። (*1 ሳሙኤል 30: 6ን ተመልከቱ።)*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት ሁለትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. የእስጢፋኖስን ሞት ተከትሎ ክርስቲያኖች በስፍራ ሁሉ ተበተኑ። አንዳንዶቹ ወደ አንጾኪያ መጡ።<br>2. ስለ ኢየሱስ የምስራቹን ቃል አሰራጩ። ብዙዎች አመኑ። ሕይወታቸውን ለጌታ ሰጡ።<br>3. አዳዶስ ክርስቲያኖችን እንዲረዳቸው በርናባስ ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ ተላከ። ይህ ከባድ ኃላፊነት መሆኑ ስለገባ ከእርሱ ጋር ሳውልን ይዞ ሄደ። በአንጾኪያ በሚገኙ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትም ለአንድ ሙሉ አመት አስተማሩ።<br>4. በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ለሌላ አዲስ ስራ እንዲልኳቸው ቤተ ክርስቲያንን ተናገረ።<br>5. ኤልማስ ከሚባል ጠንቋይ ተቃውሞ ወደ ገጠማቸው ቆጵሮስ ወደ ሚባል ቦታ ተጓዙ። ኤልማስ አገረ ገዢውን በኢየሱስ ከማመን ለመከልከል ሞከረ። ሳውል ሲናገረም ኤልማስ ታወረ። አገረ ገዢውም በኢየሱስ አመነ።<br>6. ቃሉን በወንጌል ስርጭት ስራ ውስጠ የመስበክ አስፈላጊነትን አፅንኦት ሰጥታችሁ ተናገሩ። (*የሐዋርያት ስራ 11: 19-20*).<br>7. እንደክርስቲያን የማደግ አስፈላጊነትን አስረዱ። (*1ኛ ጴጥሮስ 2: 2*).<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሁለትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | የሳውልን ሞዴል ተጠቅማችሁ በክርስትና ሕይወት የሚገጥሙ ችግሮችን ተወያዩባቸው። | የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተጠቅማችሁ የዛሬውን ትምህርት ከልሱ።<br>1. የጳውሎስና የበርናባስ ተልእኮ የተሳካ ነበር? መልሶቻችሁን ግለጹ።<br>2. ከኤልማስና ከጳውሎስ ፍጥጫ ስለእግዚአብሔር ኃይል ምን ትምሕርቶችን መማር እንችላለን? |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. ሰዎች ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ ሕይወት ችግር አልባ እንዲሆን ይጠብቃሉ። ይህ አይነቱ እምነት ላላቸው ሰዎች ጳውሎስ ምን ምክር የሚሰጣቸው ይመስላችኋል? ***2ኛ ቆሮንቶስ 11: 23-33***ን ተመልከቱ።<br>2. በችግር ውስጥ እያለፉ ላሉ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር እንዲያበረታቸው ጸልዩላቸው። በችግር ውስጥ እያለፈ ያለ ክርስቲያንን ማስታወስ ትችሉ ዘንድ የመጽሐፍ ገጽ ማውጫ አዘጋጁ። | **ትምሕርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. በአገልግሎታቸው ስላዮቸው አስደናቂ የሰዎች ሕይወት ለውጦች ለተማሪዎቻችሁ ሊነግሯቸው የሚችሉ ሰባኪዎችን ከተማሪዎቻችሁ ጋር እንድታገናኟቸው ይሁን። ተማሪዎቻችሁም ይህንኑ በማስታወሻ መዝገበው ምን ያህል ሕይወታቸውን እንደፈተሸው ጠይቋቸው።<br>2. የተሻለ የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤን ማዳበር እንዴት እንደሚቻል አንድ ክርስቲያን መሪ ጠይቁ። ከዚያም ከእርሱ ያገኛችሁትን ምክር መጽሐፍ ቅዱስን የበለጠ ለመረዳት የምትችሉበትን መንገድ አዳብሩ። |

| | ሀ9 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – ሰባኪው | ሀ9 - ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – የሐዋርያው ጳውሎስ<br>ርዕስ – ስብከቶቹ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 13: 1-12*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *የሐዋርያት ስራ 13: 12*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. *መንፈስ ቅዱስ በስራ ላይ ነው። የወንጌሉ የምስራች ቃል በብዙ አዳዲስ ስፍራዎች ይሰራጭ ነበር።*<br>2. *ወንጌልን የሚቃወም ሰይጣናዊ አሰራር አለ።* | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 13: 13-52*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *የሐዋርያት ስራ 13: 49*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. በኢየሱስ ክርስቶስ ዙሪያ ያሉ መልእክቶች አብዛኞቹ መሠረታቸው ብሉይ ኪዳን ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ሞቱና ትንሳኤው በእግዚአብሔር እቅድ መሠረት የተፈጸመ ክስተት ነው።<br>2. የኃጢአት ይቅርታ የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ ነው። |
| *መግቢያ* | የእግዚአብሔርንና የሰይጣንን ጥል/ግጭት ለተማሪዎቻችሁ አስተዋውቁ። ይህንንም በኤደን ገነት ውስጥ ከተፈጸሙ ድርጊቶች ጋር አገናኙነት። ከዚያም የሰውን የውድቀት ታሪክ ተወያዩበት። ሰይጣን በተለያዩ መልኮች በንቃት የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል እንዳይሰበክ ለማድረግ እንደሚሰራ ጠቁሟቸው። | ተማሪዎቻችሁን ስለይቅርታ አስፈላጊነት እንዲያስቡ ጠይቋቸው። አንድን ሰው ይቅር ለማለት ስለሚያስችሏቸው እድሎች እንዲያስቡ አድርጓቸው። የእግዚአብሔር ይቅርታ እንደሚያስፈልገን አሰላስሉ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በክርስትና የኃጢአት ይቅርታ መልእክቶች መካከል መሆኑን ተወያዩበት። ስለይቅርታ ትክክል ያልሆኑ ሐሳቦችን አንስታችሁ ተወያዩ። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. የእስጢፋኖስን ሞት ተከትሎ ክርስቲያኖች በስፍራ ሁሉ ተበተኑ። አንዳንዶች ወደ አንጾኪያ<br>2. ስለኢየሱስ ክርስቶስ መልካሙን ዜና አሰራጩ። ብዙዎችን በኢየሱስ አመኑ። ፊታቸውንም ወደ ጌታ አዞሩ።<br>3. በርናባስ ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ እነኚህ አዲስ ክርስቲያኖችን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲረዳቸው ተላከ። ይህ ትልቅ ኃላፊነት መሆኑን ስለተገነዘበ ከእርሱ ጋር ሳውልን ወደ አንጾኪያ ይዞ ተጓዘ። ለአንድ አመት ያህልም በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን እየተዘዋወሩ አስተማሩ።<br>4. በዚያን ወቅት መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን በርናባስንና ሳውልን ለሌላ አዲስ ስራ እንድትልክ ተናገራት።<br>5. ቆጵሮስ ወደ ሚባል አገር ሲደርሱ ኤልማስ ከሚባል ጠንቋይ ተቃውሞ ገጠማቸው። ይህ ጠንቋይ አገረ ገዢውን ክርስቲያን እንዳይሆን ለመከልከል ጥረት አደረገ።<br>6. ሳውል ተናገረ። ኤልማስም ያን ጊዜ እውር ሆነ። አገረ ገዢውም በኢየሱስ ክርስቶስ አመነ።<br>7. *በአጋንንት መያዝ ማለት ምን ማለት ነው?*<br>8. *የወንጌል መልዕክት በዚያን ዘመንና በዚህ ዘመን እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ ተወያዩበት።*<br>9. *የእግዚአብሔር ፍርድ ለምን በኤልማስ ላይ እንደመጣበት ገምቱ።*<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት ሶስትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ አሁን ወደ ሌላኛው ቆጵሮስ መጣ።<br>2. በመጀመሪያ መልእክቱ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት፣ ሞቱንና ትንሳኤውን አስመልክቶ በአይሁድ ታሪክ ውስጥ ያለውን ዝርዝር መረጃ ሰጣቸው። በመጨረሻም "በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሆነ የኃጢአት ስርየት ዛሬ ለእናንተ ታወጆላችኋል።" በማለት ደመደመ። *(**ቁጥር 38**)*<br>3. በምኩራብ ውስጥ ከሰበከው ከመጀመሪያው ስብከት በኋላ በሚቀጥለው ሰንበት ተመልሶ እንዲመጣ ተጋበዘ።<br>4. በሚቀጥለው ሰንበትም ሁሉም የከተማይቱ ነዋሪ ጳውሎስን ለመስማት ወጣ። ይህም አይሁዳውያንን አስቀናቸው።<br>5. ጳውሎስም እነርሱ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ስላልፈለጉና ስለተቃወሙ ለአሕዛብ ለመስበክ መገደዱን ነገራቸው። ኢሳያስ ***49: 6.***<br>6. *የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስ እንዲሞት ለምን እንደፈለጉ ግለጹ።*<br>7. *ለምን ኢየሱስ መሞት እንደነበረበት እንዲሁም ሞቱና ትንሳኤው የእግዚአብሔር እቅድ እንደነበረ አሰላስሉ።*<br>8. *ክርስቶስን እንደአዳኝነት ልዩ ስለመሆኑ አሰላስሰሉ። (**ቁጥር 38-39**)*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሶስትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | አሁን በተማርነው ትምህርት እግዚአብሔር ሰይጣንን እንዴት እንዳሸነፈው እንዲያብራሩላችሁ ጠይቋቸው። | የዛሬውን ትምህርት ለመከለስ የሚረዳ ሙከራ ለተማሪዎቻችሁ ስጧቸው። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. አገረ ገዢውና ኤልማስ ለወንጌል መልእክት የሰጡትን ምላሽ አነጻ ፅሩት። ተማሪዎቻችሁንም ለወንጌል ስለሰጡት ምላሽ በመጠየቅ ፈትሿቸው።<br>2. ዛሬ በማህበረሰቡ ውስጥ በሚታዩ ፊልሞች ዋነኛው ሀሳብ ምን እንደሆነ ይታወቃል። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደአዳኝነቱ ልዩ መሆኑ በባሕላችን ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ ምንድነው?<br>2. **ኤፌሶን 4:32**ን አንብቡ። በዚህ ክፍል ጳውሎስ ስለይቅርታ ያለው በተማሪዎች ሕይወት ላይ ምን ተፅእኖ እንዳለው ተወያዩበት። |

| | ሀ9 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 – የሐዋርያው ጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – 'የተከፈለች ከተማ' | ሀ9 - ደረጃ 4<br>ጥናት 4 – የሐዋርያው ጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – ቃል ኪዳኖቹ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***የሐዋርያት ስራ 13: 13-16; 42-52***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***የሐዋርያት ስራ 13: 49***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. *የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ጠቃሚ ነው።*<br>2. *የኢየሱስ ክርስቶስ መልዕክት ለሁሉም ሰው ነው። ለተቀበሉት ሁሉም ደስታን አመጣላቸው።* | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***የሐዋርያት ስራ 14: 1-28***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ማርቆስ 16: 20***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. የኢየሱስ ክርስቶስ መልዕክት ሰዎችን ይከፍላል። እንዲሁም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሚሰበከው መልክእክት ሰዎች የሚሰጡት ምላሽ አንዳንድ ገዜ ከባድ ነው።<br>2. ልክ ጳውሎስ ያሳየውን አይነት ለክርስቶስ ታማኝ መሆን በጣም አስፈላጊ ነው። |
| *መግቢያ* | *መጽሐፍ ቅዱስ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ተማሪዎቻችሁን ጠይቋቸው። (በዚህ ጥናት ውስጥ "ጌታ" የሚለው ቃል ለምን ያህል ጊዜ እንደተጠቀሰ እዩ።) የመጽሐፍ ቅዱስ መካከለኛ መልእክቱ ለሰዎች ሁሉ ስለሆነው ስለ ክርስቶስ እንደሆነ ለተማሪዎቻችሁ አስተዋውቋቸው። ክርስቲያኖች የመጡት ከተለያዩ ባሕላዊ አካባቢዎች መሆኑን አስታውሷቸው።* | *"ታማኝ" የሚለውን ቃል ትርጉም ተማሪዎቹ እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው። ለዚህም በትንንሽ ነገሮች ውስጥ የታማኝነት ምሳሌዎችንና ታማኝ የሆኑ ሰዎችን ምሳሌዎች እንዲሰጧችሁ ጠይቋቸው። ታማኝነት ለምን አስፈላጊ እንደሆነ አስቡ።* |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ አሁን ጲስዲያ ተብሎ ወደ ሚጠራው ሌላኛው የአንጾኪያ ክፍል መጣ። በምኩራብ ውስጥ ከሰበከው ከመጀመሪያው ስብከት በኋላ በሚቀጥለው ሰንበት ተመልሶ እንዲመጣ ተጋበዘ።<br>2. በሚቀጥለው ሰንበትም ሁሉም የከተማይቱ ነዋሪ ጳውሎስን ለመስማት ወጣ። ይህም አይሁዳውያንን አስቀናቸው።<br>3. ጳውሎስም እነርሱ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ስላልፈለጉና ስለተቃወሙ ለአሕዛብ ለመስበክ መገደዱን ነገራቸው። **ኢሳያስ *49: 6.***<br>4. *የጳውሎስን አድማጮች አተኩሩባቸው። (**ቁጥር 16, 42, 43 እና 48**)*<br>5. ለምንድነው ወንጌል በመጀመሪያ ለአይሁድ መሰበክ የነበረበት?<br>6. የእግዚአብሔር ቃል እንዴት እንደተሰራጨ አስረዱ። (***ቁጥር 49***)<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስና በርናባስ ወደ ኢቆንዮን ሲመጡ ብዙ አሕዛብና አይሁዳውያን አመኑ። ጥቂት አይሁዳውያን ግን በእነርሱ ተቃውሞ አስነሱባቸው።<br>2. ከተማይቱ በዚህ የወንጌል መልእክት ምክንያት ለሁለት ተከፈለች። ነገር ግን አንዳንዶች ጳውሎስንና በርናባስን በድንጋይ ለመውገር አሴሩ። ስለዚም ጳውሎስና በርናባስ ወደ ልስጥራን ሸሹ።<br>3. በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር በጳውሎስ አማካኝነት አንድ ሽባ ሰው እንዲፈወስ አደረገ። ውጤቱም የዚያች ከተማ ሰዎች ጳውሎስና በርናባስ አማልክት ናቸው ብለው እንዲያስቡ አደረጋቸው። ስለዚህም ለእነርሱ መስዋእትን ለማቅረብ ፈለጉ።<br>4. ጳውሎስና በርናባስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ምንም ከማይጠቅሟቸው ጣዖቶቻቸው አላቀው ወደ እውነተኛው ሕያው እግዚአብሔር ሊያቀርቧቸው እየሞከሩ መሆኑን ነገሯቸው። እግዚአብሔር የሰጠንን ነገሮች ሁሉ ነገሯቸው። ***(ቁጥር 17)***<br>5. አይሁዶች ከአንጾኪያና ከኢቆንዮን መጡ። ሕዝቡንም ጳውሎስን በድንጋይ እንዲወግሩት አሳመኗቸው። ከከተማ ውጪም ጎትተው አወጧቸው። በድንጋይም ወገሩት። የሞተ ስለመሰላቸውም ትተውት ሄዱ። ጳውሎስ ግን አልሞተም። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን። በሚቀጥለው ቀንም ደርቤ ወደ ሚባል ቦታ ተጓዙ። በዚህ ስፍራም ብዙዎች ደቀ መዝሙር ሆኑ።<br>6. ለሕይወታቸው ሳይሳሱ ወደ ልስጥራንና አንጾኪያ ተመልሰው ክርስቲያኖችን አበረታቱ። በዚህም ሕይወታቸውን ለአደጋ ጥለው<br>7. ***በቁጥር 15 – 17** የእግዚአብሔር ማንነት ላይ አተኩራችሁ ተወያዩ።*<br>8. *እንደጳውሎስና በርናባስ የመፅናት አስፈላጊነትን ተወያዩበት። **ቁጥር 22ን** በትኩረት እዩት።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | በተማርነው ትምህርት ውስጥ እግዚአብሔር ሰይጣንን እንዴት እነዳሸነፈው በማብራራት ትምህርቱን አጠቃሉት። | ለተማሪዎች ሙከራ በመስጠት የዛሬውን ትምህርት አጠናቁት።<br>1. በቁጥር 3 ውስጥ እንደምናየው የተአምራትና ድንቆች አላማ ምን ነበር? ***ቁጥር 3?***<br>2. ጳውሎስና በርናባስ ለእግዚአብሔር ታማኝነታቸው በሚገባ አሳይተዋል? እግዚአብሔር ለእርሱ ስራ ሕይወታችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይፈልጋል? |
| ከሕይወት ጋር<br>*ማዛመድ* | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. በቁጥር **42 እና 48** ላይ አሕዛብ ለወንጌል መልእክት የሰጡትን ምላሽ እዩ። ከዚህ ለወንጌል መልእክት ስለሚሰጥ ምላሽ ምን እንማራለን?<br>2. በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ላሉ ሰዎች ወንጌልን ለማወጅ ስለሚሞክር የሚሺነሪዎች ማህበረሰብ ጥናት አካሂዱ። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. በቡድን ሆናችሁ "ታማኝ" አንድ እንቆቅሽ ሥሩ።<br>2. በዛሬው ሕይወታችን ውስጥ ያሉ ጣኦታትን የክርስቶስ መልእክት ምን ያህል ይሚገታቸዋል? |

| | ሀ10 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – ስለጌታ መከራን መቀበል | ሀ10 - ደረጃ 4<br>ጥናት 1 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – ጳውሎስ በፊልጵስዩስ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 14: 1-21*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *1 ጴጥሮስ 4: 16*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ክርስቲያኖች አንዳንድ ጊዜ በእምነታቸው ምክንያት መከራ ይደርስባቸዋል። ነገሮች እየከፉ ሲሄዱ "ተስፋ መቁረጥ" የለባቸውም።<br>2. ክርስቲያኖች ሁሉን ነገር በልግስና በሚሰጣቸውና የሁሉ ነገር ፈጣሪ በሆነው በሕያው እግዚአብሔር ማመን አለባቸው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 16: 9-40*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *የሐዋርያት ስራ 16: 31*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. የእግዚአብሔርን ምሪት መስማትና መታዘዝ አስፈላጊ ነው።<br>2. እግዚአብሔር የሰዎችን ልብ ይከፍታል። ሰዎች የሚድኑትም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። |
| መግቢያ | ሁሉን በሰራ በእግዚአብሔር ማመን ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ተነጋገሩበት። በእግዚአብሔር ፊት ስላለብን ኃላፊነትና ተጠቀያቂነት ዙሪያ ውይይት አካሂዱ። | እኛ ሁላችን ለምን መዳን እንደሚገባን ጥያቄ ጠይቁ። የእግዚአብሔርን የማዳን ባሕርይ ግለጹ። እንዲሁም በራሳችን ስራ ሳይሆን እንዴት እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ባደረገው ስራ መዳን እንደቻልን አስረዷቸው። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስና በርናባስ ወደ ኢቆንዮን ሲመጡ ብዙ አይሁዳውያንና አሕዛብ አመኑ። ነገር ግን ጥቂት አይሁዳውያን ተቃውሞ አስነሱ።<br>2. በወንጌል ምክንያት ከተማይቱ በሁለት ተከፈለች። ነገር ግን አንዳንዶች ጳውሎስንና በርናባስን በድንጋይ ለመውገር አሴሩ። ስለዚህ ጳውሎስና በርናባስ ወደ ልስጥራን ሄዱ።<br>3. በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር በጳውሎስ አማካኝነት አንድ ሽባ ሰው እንዲፈወስ አደረገ። ውጤቱም የዚያች ከተማ ሰዎች ጳውሎስና በርናባስ አማልክት ናቸው ብለው እንዲያስቡ አደረጋቸው። ስለዚህም ለእነርሱ መስዋእትን ለማቅረብ ፈለጉ።<br>4. ጳውሎስና በርናባስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ምንም ከማይጠቅሟቸው ጣዖቶቻቸው አላቀው ወደ እውነተኛው ሕያው እግዚአብሔር ሊያቀርቧቸው እየሞከሩ መሆኑን ነገሯቸው። እግዚአብሔር የሰጠንን ነገሮች ሁሉ ነገሯቸው።<br>5. አይሁዶች ከአንጾኪያና ከኢቆንዮን መጡ። ሕዝቡንም ጳውሎስን በድንጋይ እንዲወግሩት አሳመኗቸው። ከከተማ ውጪም ጎትተው አወጧቸው። በድንጋይም ወገሩት። የሞተ ስለመሰላቸውም ትተውት ሄዱ።<br>6. ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን። በሚቀጥለው ቀንም ደርቤ ወደ ሚባል ቦታ ተጓዙ። በዚህ ስፍራም ብዙዎች ደቀ መዝሙር ሆኑ።<br>7. ***በቁጥር 15 – 17*** *የእግዚአብሔር ማንንት ላይ አተኩራችሁ ተወያዩ።*<br>8. *እንደጳውሎስና በርናባስ የመፅናት አስፈላጊነትን ተወያዩበት። ቁጥር 22ን በትኩረት እዩት።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት 1.** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ ወደ ሌሎች የእስያ አካባቢዎች እንዳይሄድ በግልጽ ነበር መመሪያ የተሰጠው። አንድ ሌሊት ላይ ወደ መቄዶንያ እንዲሄድ በራዕይ መልእክትን ተቀበለ። (አውሮፓ)<br>2. ወንጌልን ወደ አውሮፓ ለማድረስ ምክንያቶች የነበሩትን ሁኔታዎች አስረዱ። (***ቁጥር 9***)<br>3. በፊልጵስዩስ በአንድ ላይ በወንዝ ዳርቻ ተሰብስበው የሚጸልዩ ሴቶችን ተገናኘ። በእነኝህ ሴቶች መካከልም ሊዲያ የምትባል ሴት ነበረች።<br>4. እግዚአብሔር የሊዲያን ልብ ከፈተ ስንል ምን ማለታችን ነው? አብራሩት። (***ቁጥር 14***)<br>5. ከአንድ የጥንቆላ መንፈስ ካደረባት ሴት ጳውሎስ አጋንንቱን ሲያስወጣ እርሱና ሲላስ በወህኒ ቤት ተጣሉ።<br>6. የመሬት መንቀጥቀጥ ተነሳ። እስረኞችም በሙሉ ነጻ ሆኑ። የወህኒ ጠባቂው እስረኞቹ በሙሉ ያመለጡ መስሎት ራሱን ሊያጠፋ ነበር። ጳውሎስ ማንም እንዳላመለጠ አረጋገጠለት።<br>7. የወህኒ ጠባቂው ጳውሎስን የጠየቀውን ጥያቄና ጳውሎስም ለዚህ ጥያቄ የሰጠውን መልስ አብራሩት።(***የሐዋርያት ስራ 16: 31***)<br>8. *ኢየሱስ ክርስቶስ የሰዎች ደህንነት ማዕከል እንደሆነ በትኩረት ተወያዩበት።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት 1.** |
| ክለሳ | የዛሬውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት **ከዘጸአት 20፡ 1-6** ጋር አዛምዱት። ስለሕያው እግዚአብሔር ተማሪዎች እንዲገነዘቡ እርዷቸው። ባለንበት ዘመን በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ሊገባ ስለሚችል ጣኦት ተነጋገሩ። | የዛሬውን ትምህርት በሚከተሉት ጥያቄዎች ከልሱት።<br>1. የወህኒ ጠባቂውን ተከትለው የሆኑ ነገሮች አስረዱ።<br>2. ጥምቀት ምን ማለት ነው? ለመጠመቅ ምን ያስፈልጋል? (***ቁጥር 15, 31-33***) |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. በእግዚአብሔር ፊት ስላለብን ኃላፊነት አስቡ። በክርስትና ሕይወታችን ይህ ምን ለውጥ ማስከተል አለበት?<br>. **ቁጥር 15** ስለ "ጀግና ሰዉ" አምልኮ ምን ያስተምረናል? | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. መዳን በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ መሆኑን መረዳት።<br>2. የአማኞች ጥምቀት አስፈላጊነት። |

| | ሀ10 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – የሕይወት ዘመን ወዳጅ | ሀ10 - ደረጃ 4<br>ጥናት 2 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – ጳውሎስ በቤርያና በተሰሎንቄ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 16: 1-3; 2 ጢሞቴዎስ 1: 1-5*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *2 ጢሞቴዎስ 3: 15*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. *መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና ማወቅ የደህንነት ጥበብ እንዲኖረን ይረዳናል።*<br>2. ክርስቲያን ጓደኛ በጣም ያስፈልገናል። እንዲሁም አንዳችን ለሌላችን ልንጸልይ ይገባናል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 17: 1-14*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *የሐዋርያት ስራ 17: 11*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን የተነገረለት ክርስቶስ ነው። ሞቱና ትንሳኤው በጣም አስፈላጊ ናቸው።<br>2. የክርስትና እምነትን ለመገንባት መጽሐፍ ቅዱስን መመርመርና ማወቅ አስፈላጊ ነው። |
| *መግቢያ* | ሕይወታችንን በበጎም ሆነ በመጥፎ ጎኑ ተፅዕኖ ስለሚያድርጉበት ነገሮች ተወያዩ። ክርስቲያናዊ ተፅዕኖ በሕይወታችን በጣም አስፈላጊ መሆኑን ከተማሪዎቻችሁ ጋር አብራችሁ ተወያዩ። በክርስትና ሕይወታችሁ በእናንተ ላይ በጎ ተፅዕኖ ያሳደረባችሁ ማን እንደሆነ እንዴትም በእናንተ ላይ ተፅዕኖ እንዳሳደሩባችሁ ተናገሩ። | ተማሪዎቻችሁ እጅግ በጣም አስፈላጊ ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን ሰዎችና ለምን አስፈላጊ እንደሆኑ እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው። የክርስትና መልዕክቱ ስለአንድ ሰው ብቻ መሆኑን ንገሯቸው። **በሐዋርያት ሥራ** 17፡1 – 14 ባለው ክፍል ውስጥ ያለውን መልእክት አንብቡላቸው። |
| *ማጠናቀቅ* | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ስለ ጢሞቴዎስ ቤተ ሰብ ግለጹላቸው።<br>2. የጢሞቴዎስ እናትና የሴት አያት ለጢሞቴዎስ እምነት እድገት እንዴት አስፈላጊ እንደሆኑ ግለፁላቸው።<br>3. ለክርስቲያናዊ ቤተ ሰብ ዋጋ ስጡ።<br>4. ጳውሎስ በጢሞቴዎስ ግርዘት ለምን እንዳመነ ተወያዩበት። ከዚህስ ምን ትምህርት እንማራለን?<br>5. ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ ጋር አብሮ መጓዝ ጀመረ። ለጳውሎስም ትልቅ ረዳት ሆነለት።<br>6. ለጢሞቴዎስ በጻፈለት ደብዳቤ የተጠቀመባቸውን ቃላት ተመልከቱ። *(2 ጢሞቴዎስ 1: 3-5)*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት ሁለትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ ከፊልጵስዩስ ወደ ተሰሎንቄ ተጓዘ። በዚያም በምኩራብ ገብቶ ሰበከ።<br>2. *በተሰሎንቄ በምኩራብ ውስጥ ጳውሎስ የሰበከውን ስብከት ግለጹላቸው። እንዲሁም "ክርስቶስ" የሚለውን ማዕረግ ግለጹላቸው። የዚህ ማዕረግ ትርጉሙ የተቀባ አዳኝ ማለት ነው።*<br>3. *የመልእክቱን አንደምታዎች አሰላስሉ።*<br>4. *የሚከተሉትን ቃላት አስቡባቸው። "ዓለምን ያወኩ እነዚህ ወደዚህ ደግሞ መጥተዋል"፣(**ቁጥር** 6)*<br>5. ጳውሎስና ሲላስ በድጋሚ በሌሊት ፈጥነው መልቀቅ ነበረባቸው። ከዚያም ወደ ቤርያ ተጓዙ።<br>6. በቤርያ የነበሩት አይሁዶች በተሰሎንቄ ከነበሩት አይሁዶች በጣም ይለዩ ነበር። በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን ያጠኑ ነበር። *(**ቁጥር** 11-12)*<br>7. ቢሆንም ተቃውሞ እያየለ ይሄድ ነበር። ስለዚህም ጳውሎስን ወደ አቴና ሸኙት።<br>8. ጳውሎስና ሲላስ የገጠማቸውን ተቃውሞ በዚህ ዘመን ያሉ ክርስቲያኖች በእምነታቸው ምክንያት ከሚገጥማቸው ተቃውሞ ጋር አወዳድሩት።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሁለትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | ቁልፍ ጥቅሱን አጥኑት። ከዚያም ጥቅሱ የዛሬውን ትምህርት እንዴት እንደሚያጠቃልለው ከክፍሉ ጋር ተወያዩ። | **ኢያሱ 1፡8**ን አንብቡ። ከዚያም ከቁልፍ ጥቅሱ ጋር አወዳድሩት። (***የሐዋርያት ስራ 17: 11***) እንደክርስቲያን ፈተናዎች የሚሆኑብን ነገሮች ምንድናቸው? |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. ክርስቲያን ወዳጆች የማፍራት ጥቅምን ለመረዳት።<br>2. ክርስቲያን ወዳጅነቶችን ለመሻት።<br>3. ለወዳጆቻችንና ለስጋ ዘመዶቻችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ መጸለይ። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብን ጥቅም መረዳትና አመለካከቶቻችንን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ ማድረግ። (ቁልፍ ጥቅሱን ተመልከቱ።)<br>2. ኢየሱስ ንጉስ መሆኑን ማመን በሕይወታችን ምን ለውጥ እንደሚያመጣ ማወቅ። |

| | ሀ10 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – ጳውሎስ በወህኒ ቤት | ሀ10 - ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – ጳውሎስ በአቴናና በቆሮንቶስ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 16: 16-34*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** *የሐዋርያት ስራ 16: 31*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ድነት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ የሚገኝ ነው።<br>2. የዳኑ ደግሞ መጠመቅ አለባቸው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 17: 15-34; 18: 1-18*<br><br>**Key ቁጥCs:** *የሐዋርያት ስራ 17: 30-31*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ንስሐ መግባት የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው።<br>2. እግዚአብሔር በዓለም ላይ ይፈርዳል። |
| መግቢያ | ከአንድ አደጋ ውስጥ እያለፉ ያሉ ሰዎች በአንድ ግብረ ኃይል አማካኝነት ከአደጋው ጉዳት ሳይደርስባቸው ሲድኑ የሚገልጽ ታሪክ ንገሯቸው። ለምሳሌ ያህል የእሳት አደጋ። ታሪኩንም “መዳን”፣ “አዳኝ”፣ “ድነት” የሚሉትን ቃላት ለማብራራት ተጠቀሙበት። ተማሪዎች በሕይወታቸው ድነትን ያውቁ እንደሆነ እንዲናገሩ አበረታቷቸው። | ተማሪዎቻችሁን የንስሐን ትርጉም እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው። **1ኛ ተሰሎንቄ 1:9ን** ተጠቅማችሁ የንስሐን ጽንሰ ሐሳብ አስረዱ። እግዚአብሔርን እንደአዳኝ ተቀብለን ፊታችንን ወደ እርሱ ስለማዞር በትኩረት ንገሯቸው። ይህም የቀድሞ ወይንም አሮጌ የአኗኗር ዘይቤያችንን መተውን ይጠይቃል። በወንጌል ኃይል ስለ ተለወጡ ሰዎች ምስክርነት በዚህን ጊዜ ማንሳቱና መወያየቱ የንስሐን ትርጉም ይበልጥ ለመረዳት ይጠቀማል። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ወንጌልን ወደ አውሮፓ ለማድረስ ምክንያቶች የነበሩትን ሁኔታዎች አስረዱ። (***ቁጥር 9***)<br>2. በፊልጵስዩስ በአንድ ላይ በወንዝ ዳርቻ ተሰብስበው የሚጸልዩ ሴቶችን ተገናኘ። በእነኝህ ሴቶች መካከልም ሊዲያ የምትባል ሴት ነበረች።<br>3. እግዚአብሔር የሊዲያን ልብ ከፈተ ስንል ምን ማለታችን ነው? አብራሩት። (***ቁጥር 14***)<br>4. ከአንድ የጥንቆላ መንፈስ ካደረባት ሴት ጳውሎስ አጋንንቱን ሲያስወጣ እርሱና ሲላስ በወህኒ ቤት ተጣሉ።<br>5. የመሬት መንቀጥቀጥ ተነሳ። እስረኞችም በሙሉ ነጻ ሆኑ። የወህኒ ጠባቂው እስረኞቹ በሙሉ ያመለጡ መስሎት ራሱን ሊያጠፋ ነበር። ጳውሎስ ማንም እንዳላመለጠ አረጋገጠለት።<br>6. የወህኒ ጠባቂው ጳውሎስን የጠየቀውን ጥያቄና ጳውሎስም ለዚህ ጥያቄ የሰጠውን መልስ አብራሩት።(***የሐዋርያት ስራ 16: 31*** )<br>*7. በኢየሱስ ስም ውስጥ ስላለው ስልጣን በትኩረት ተነጋገሩ። (**ቁጥር 18**)*<br>*8. አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች ኢፍትሐዊ በደል ሊደርስባቸው ይችላል። (**ቁጥር 23**)*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት ሶስትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ አቴና ደረሰ። የጓደኞቹን መድረስ እየተጠባበቀም ወዲያና ወዲህም በመዘዋወር ላይ ነው። በሚያያቸው በርካታ ጣኦታት ምክንያት መንፈሱ ተበሳጨበት።<br>2. በገበያና በምኩራብ ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ መስበክ ጀመረ።<br>3. ጳውሎስ ከዚያ ወደ ከተማይቱ ማዕከላዊ ስፍራ ተወስዶ ስለሚሰብከው ስለዚህ አዲስ ትምህርት ገለጻ ተጠየቀ።<br>4. ጳውሎስ አለምን ስለሰራውና ታላቅ ስለሆነው ፈጣሪ ስለ እግዚአብሔር ተናገረ። ሆኖም ይህ ታላቅ አምላክ ከእኛ ከሁላችን ሩቅ እንዳልሆነ ገለጸ። እንዲሁም እግዚአብሔር ከሙታን ባስነሳውና በሾመው ልጁ አማካኝነት በአለም ላይ እንደሚፈርድ ገለጸላቸው።<br>5. ስለ ትንሳኤ ሲያወራ አብዛኞቹ አላገጡበት። ጥቂቶች ግን አመኑ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ጳውሎስ ከዚያ ተነስቶ ወደ ቆሮንቶስ ተጓዘ።<br>6. በዚያም አቂላንና ጵርስቅላን ተገናኛቸው። ረዳቱም ሆኑለት። በቆሮንቶስ ለአስራ ስምንት ወራት ቆየ። ብዙ ሰዎችም አማኞች ሆኑ።<br>7. ***የሐዋርያት ስራ 18: 9*** - እግዚአብሔር ጳውሎስ በቆሮንቶስ ምንም አደጋ እንደማይገጥመው ማረጋገጫ ሰጠው።<br>*8. **በቁጥር 24 – 31** ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ምን እንዳስተማረ በትኩረት አስረዱ።*<br>*9. ፍርድ ምን ማለት እንደሆነ አስረዷቸው።*<br>*10. በአቴናና በቆሮንቶስ ሰዎች ለጳውሎስ መልዕክት ምላሻቸው ምን እንደነበረ አሰላስሉ።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሶስትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | በጳውሎስና ሲላስ የፊልጵስዩስ ታሪክ የግራፊቲ ቦርድ ፍጠሩ። | የጳውሎስን የአቴና ስብከት አቀራረብና የቆሮንቶስ ስብከት አቀራረብ አወዳድሩ። ልዩነት አለ? ለምን? |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. ድነት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት መሆኑን የማወቅ አስፈላጊነት።<br>2. በጥምቀት ከኢየሱስ ጋር ስለመመሳሰል። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. ስለንስሓ አስፈላጊነትና ክርስቲያን እንዴት በየቀኑ ከኃጢአት መራቅ እንዳለበት።<br>2. ለሌሎች ወንጌልን ስለመንገርና አንድ ቀን እግዚአብሔር በአለም ላይ እንዴት እንደሚፈርድ። |

| | ሀ10 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – የአቴና ከተማ | ሀ10 - ደረጃ 4<br>ጥናት 4 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – ጳውሎስ በኤፌሶን |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 17: 10-34*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *የሐዋርያት ስራ 17: 30*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. እግዚአብሔር ምድርን የፈጠረ ሕያው እግዚአብሔር ነው።<br>2. እግዚአብሔር ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ ትዕዛዝን ሰጥቷል።<br>3. እግዚአብሔር በጽድቅ በአለም ላይ ይፈርዳል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 19: 1-41*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *ኤፌሶን 2: 8-9*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. የእግዚአብሔር ስራና የእግዚአብሔር ቃል በኤፌሶን ተሰራጩ።<br>2. የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ገነነ። |
| መግቢያ | ጣኦት ስለሚለው ቃል ስላላቸው መረዳት ተማሪዎቻችሁን ጠይቁ። ጣኦት የሚለውን ቃል እንዴት ይገልፁታል? **በዘጸአት 20** ውስጥ ያሉትን የመጀመሪያዎቹን ሁለት ትዕዛዛት ተወያዩባቸው። በ**1ኛ ተሰሎንቄ 1፡ 9** መሠረት የንስሐን ትርጉም አብራሩላቸው። | በጥናት ሶስት የተማሩትን ትምህርት ከልሱላቸው። ስለንስሐ አሰላስሉ። እንዲሁም በየዕለት ሕይወታችን ንስሐ ምን ማለት እንደሆነ ተወያዩበት። ንስሐ የአኗኗር ዘይቤ ለውጥን እንደሚያስከትል ግንዛቤን አዳብሩ። በ*ሐዋርያት ስራ 19: 18-20* ላይ ውይይት አካሂዱ። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ አቴና ደረሰ። የጓደኞቹን መድረስ እየተጠባበቀም ወዲያና ወዲህም በመዘዋወር ላይ ነው። በሚያያቸው በርካታ ጣኦታት ምክንያት መንፈሱ ተበሳጨበት።<br>2. በገበያና በምኩራብ ጳውሎስ ስለኢየሱስ መስበክ ጀመረ።<br>3. ጳውሎስ ከዚያ ወደ ከተማይቱ ማዕከላዊ ስፍራ ተወስዶ ስለሚሰብከው ስለዚህ አዲስ ትምህርት ገለጻ ተጠየቀ።<br>4. ጳውሎስ አለምን ስለሰራውና ታላቅ ስለሆነው ፈጣሪ ስለ እግዚአብሔር ተናገረ። ሆኖም ይህ ታላቅ አምላክ ከእኛ ከሁላችን ሩቅ እንዳልሆነ ገለጸ። እንዲሁም እግዚአብሔር ከሙታን ባስነሳውና በሾመው ልጁ አማካኝነት በአለም ላይ እንደሚፈርድ ገለጸላቸው።<br>5. ስለትንሳኤ ሲያወራ አብዛኞቹ አላገጡበት። ጥቂቶች ግን አመኑ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ጳውሎስ ከዚያ ተነስቶ ወደ ቆሮንቶስ ተጓዘ።<br>*6. **በቁጥር 24 – 31** ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ምን እንዳስተማረ በትኩረት አስረዱ።*<br>*7. የኢየሱስን ትንሳኤ ጠቀሜታ አስምሩበት።.* (***ቁጥር 31***)<br>*8. ለጳውሎስ ስብከት በተሰጡ ምላሾች ላይ ውይይት አካሂዱ።* (***ቁጥርs 32-34***)<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ አሁን በኤፌሶን ይገኛል። በዚያም እስካሁን መንፈስ ቅዱስን ያልተቀበሉ ደቀ መዛሙርት ን ያገኛል።<br>2. ጳውሎስ የዮሐንስን ደቀ መዛሙርት ማጥመቅ ለምን እንዳስፈለገው ግለጹላቸው።<br>3. አይሁዳውያን በምኩራባቸው እንዳይሰበክ ከከለከሉት በኋላ ጳውሎስ በከተማይቱ በሚገኝ የማስተማሪያ አዳራሽ ስብከቱን ቀጠለ። በዚያም ለሁለት አመት ቆየ።<br>4. እግዚአብሔር በጳውሎስ ውስጥ እያለፈ ታላላቅ ተአምራትን አደረገ። (***ቁጥር 11***) በውጤቱም መንፈስ ቅዱስ በጳውሎስ አማካኝነት መታየት ጀመረ። ብዙዎችም አመኑ። እምነታቸውንም በይፋ ገለጹ። ምን እንዳደረጉ ግለጹላቸው።<br>5. በኤፌሶን ስለተቀሰቀሰው የሕዝብ አመጽ ምክንያቶች በአጭሩ አብራሩላቸው። *(**ቁጥር 23-41**)*<br>6. *"የእግዚአብሔር መንግስት" ምን ማለት እንደሆነ ግለጹላቸ። (**ቁጥር 8**)*<br>7. *የእግዚአብሔር ቃል በኤፌሶን እንዴት እያየለ እንደመጣ አስረዱ። (**ቁጥር 20**)*<br>8. *አዳዲስ ክርስቲያናች የቀድሞ ልማዶቻቸውን በተመለከተ ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ተወያዩበት።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | በቡድን እንዴት ክርስቲያናዊ መልእክት በማህበረሰቡ ውስጥ በሚያነጋግር መልኩ እንዴት ሊሰራጭ እንደሚችል ተወያዩ። ይህን በወንጌል ስርጭት ተግባር አማካኝነት አዳብሩት። | "ወንጌል ወደ ኤፌሶን መጣ" በሚል ርዕስ የአእምሮ ካርታ ሳሉ። **በሐዋርያት ስራ 19** ያሉ ክንዋኔዎችን በጋዜጣ መልክ ሪፖርት ጻፉ። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. ስለግል ንስሐ። በንስሐ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ምን ማለት ነው?<br>2. የወንጌል ስርጭት አስፈላጊነት። የወንጌልን መልእክት ሌሎች የማጋራት አስፈላጊነት። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. የክርስቲያኖች እምነት "መንገዱ" ተብሎ ይታወቃል። *(**ቁጥር 9**)* ምን ማለት ነው? እንዴት ነው ይህ ለእኛ ፈታኝ የሚሆነው?<br>2. **በቁጥር 35 – 41** መሠረት ስለሚኖረን ማህበረሰባዊ ኃላፊነት የከተማይቱ ጸሐፊ ካደረጋቸው ነገሮች ምን አይነት ተግባራዊ ትምህርቶችን እንማራለን? |

| | ሀ11 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – ለሌሎች ማጋራት | ሀ11 - ደረጃ 4<br>ጥናት 1 – የጳውሎስ መመርመር<br>ርዕስ – ኢየሩሳሌምና የተቀሰቀሰው የሕዝብ አመፅ። |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 18: 1-11*<br><br>Key ቁጥርs: *የሐዋርያት ስራ 18: 9-10*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ጳውሎስ በሄደበት ሁሉ መልዕክቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው የሚል ነበር።<br>2. እግዚአብሔር ከጳውሎስ ጋር ነበር። በራዕይ ተገልጦለት አጽናናው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 21: 17-40; 22: 1-30*<br><br>Key ቁጥርs: *የሐዋርያት ስራ 22 : 14 እና 15*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ጳውሎስ በመቅደስ ውስጠ ከታሰረ በኋላ ለተሰበሰበው ሕዝብ ምስክርነቱን ሰጠ።<br>2. አሕዛብ ወንጌልን መቀበላቸው አይሁዳውያንን አላስደሰታቸውም።<br>3. ጳውሎስ መገረፍ ሲጀምር የሮም ዜጋ መሆኑን ነገራቸው። |
| መግቢያ | እግዚአብሔር በሕይወታችሁ እናንተን እንዴት እንዳበረታታችሁ ለተማሪዎቻችሁ ተሞክሯችሁን አጋሯቸው። በክርስትና ሕይወት ማበረታታት (ማጽናናት) አስፈላጊነቱ ምን እንደሆነ ተወያዩበት። ተማሪዎቻችሁም ከዚህ በፊት የተለማመዷቸውን የመጽናናት ምሳሌዎችን እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው። | ጳውሎስ ኢየሩሳለም ሲደርስ የገጠመውን ተቃውሞ በአጭሩ አብራሩላቸው። መከራን ሳይፈሩ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመሰከሩ ክርስቲያኖች ምሳሌዎችን ስጧቸው። ክርስቲያን ይህን ለምን ማድረግ እንዳለበት ጠይቋቸው። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ ቆሮንቶስ ደረሰ። በዚያም ጵርስቅላንና አቂላን አገኛቸው። ረዳቶቹም ሆኑለት።<br>2. እንደልማዱም ወደ ምኩራብ በሰንበት ሄዶ አይሁዳውያን ኢየሱስ ሲጠብቁት የነበረው መሲህ እንደሆነ ለማሳመን ሞከረ።<br>3. አይሁዳውያን ሲቃወሙት ደግሞ አሕዛብን ይሰብካቸው ጀመረ። ብዙዎች አመኑ ተጠመቁም።<br>*4.* *18: 9* - እግዚአብሔር ጳውሎስን በቆሮንቶስ ከእርሱ ጋር እንደሚሆንና እንደሚጠብቀው ቃል ገባለት። ይህ ለጳውሎስ እንዴት ትልቅ መጽናናትን እንዳመጣለት ንገሯቸው።<br>*5. ጳውሎስ እንዴት መልዕክቱን እንዳሰራጨ አተኩሩበት። **(ቁጥር 4 እና 11)***<br>*6. የእግዚአብሔር ቃል በቆሮንቶስ እንዴት እንደተስፋፋና የጥምቀት ጥቅምን አስረዱ።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አንድን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ደረሰ። ወደ ምኩራብም ሄደ። በሐሰትም አይሁዳዊ ያልሆነ ሰው (አሕዛብ) ወደ መቅደስ ይዞ ገባ የሚል ክስ ቀረበበት። በመቅደስ ውስጥም የሕዝብ አመጽ ተቀሰቀሰ።<br>2. ሮማዊው መኮንን በአመጽ የሚሳተፈው ሕዝብ በጳውሎስ ላይ ሊያደርስበት ከሚችለው አደጋ ካዳነው በኋላ በወታደራዊ ሰፈር ውስጥ ባለው የመወጣጫ ደረጃ ላይ ቆሞ ለሕዝቡ እንዲናገር እድል ተሰጠው።<br>3. ጳውሎስ ግልጽ የሆነ ምስክርነት ሰጠ። *(22: 1-21)* ለአሕዛብ መላኩን ሲገልጽ ሌላ የሕዝብ አመጽ ተቀሰቀሰ።<br>4. ወደ ወታደራዊ ሰፈር ተወስዶ ሊገረፍ ሲል ሮማዊ መሆኑን በመግለጹ ከመገረፍ ዳነ። በዚህ ሁኔታም ወንጀል ለመፈጸሙ ማስረጃ እስካልቀረበበት ድረስ መገረፍ አይችልም ማለት ነው።<br>5. ጳውሎስ ለምን ወደ መቅደስ እንደሄደ አተኩሩበት።<br>6. የጳውሎስን መለወጥ አተኩሩበት።<br>7. የተሰበሰበው ሕዝብ ጳውሎስን የተቃወመው ለምን እንደሆነ ግለጹ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አንድን አጠናቁ።**<br>**ጥናት አንድን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | በሙከራ የዛሬውን ታሪክ ከልሱ። | ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ወደ ሚገኘው መቅደስ መሄዱ ብልህነት መሆን አለመሆኑን ተማሪዎች እንዲከራከሩበት አድርጉ። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | ***ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?***<br>1. ***በመዝሙር 23*** መሠረት የእግዚአብሔር አብሮነት ተስፋ እንዴት እንደሚያጽናናን ተወያዩበት።<br>2. ከሰዎች ጋር አብሮ በመሆን እንዴት ማጽናናት እንደምንችል አሰቡ። ይህን ተውኑት። | ***ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?***<br>1. በየቀኑ ክርስቲያኖች በተለያዩ የአለም ክፍሎች ይታሰራሉ። የሚሰደዱና የሚታሰሩ እንዲሁም መከራ የሚደርስባችንና የሚንገላቱ ክርስቲያኖችን አስመልክቶ መደበኛ የጸሎት ጊዜ አዘጋጁ።<br>2. ልጆች ያለፈውን ሳምንት እንዴት እንዳሳለፉት እንዲገመግሙ ጠይቋቸው። ስለኢየሱስ ክርስቶስ ሊመሰክሩባቸው የሚገቡ እድሎችን ሳይጠቀሙባቸው ቀርተው እንደሆነ ጠይቋቸው። መመስከርን አስመልክቶ እግዚአብሔር ታማኞች እንዲሆኑ እንዲረዳቸው መጸለይ እንዳለባቸው ንገሯቸው። |

| | ሀ11 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – ጳውሎስን ለመግደል የተወጠነ ሴራ | ሀ11 - ደረጃ 4<br>ጥናት 2 – የጳውሎስ መመርመር<br>ርዕስ – ቂሳሪያና ገዢዎቿ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 23: 10-24; 24: 22-27*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *መዝሙር 18: 30*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. አይሁዳውያን ሊገድሉት ሲሞክሩ እግዚአብሔር አጽናናው።<br>2. ጳውሎስ ታስሮም እንኳን ወንጌልን በታማኝነት መመስከሩን ቀጠለ። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 23: 23-26; 24: 1-27; 25: 1-12*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *1 ጴጥሮስ 3: 15*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ጳውሎስ ለደህንነቱ ሲባል ወደ ቂሳሪያ ተወሰደ። በዚያም ሆኖ ለቄሳር ይግባኝ አለ።<br>2. በተለያዩ ምርመራዎች ወቅት ጳውሎስ ስለጽድቅ፣ ራስን ስለመግዛትና ስለሚመጠው ፍርድ ቀን ሰበከ። *(24: 25)* |
| መግቢያ | በጳውሎስ ዘመን የሮማ መንግስት ስለነበረው ስልጣን ለተማሪዎቻችሁ አስረዷቸው። ጋሻ ምን እንደሆነ አስረዷቸው። ከጥንት የግሪክና ሮማ አለም ባላጋሻ ወታደሮችን ምስል አቅርቡ። ጌታ እንዴት የሕዝቡ ጋሻ እንደሆነ ግለጹላቸው። ቁልፍ ጥቅሱን እንዲያጠኑት አበረታቷቸው። – ***መዝሙር 18: 30.*** | ማርቲን ሉተር በ1521 ዓ.ም. ስለኢየሱስ ክርስቶስ ሳይናወጥ ጸንቶ መቆሙን ከዚህ ታሪክ ጋር አዛምዱት። በዚያን ጊዜ ማርቲን ሉተር የተናገረውን አረፍተ ነገር በአንድ ላይ እዩት። “ጥሩ ምክንያት ከሌለኝና መጽሐፍ ቅዱስ ካላሳመነኝ በስተቀር ሕሊናዬ የእግዚአብሔር ቃል ምርኮኛ ነው። ዛሬም ይሁን ወደፊት ሕሊናዬን አልቃወምም። ሕሊናን መቃወም ትክክል አይደለም። ለአደጋ ተጋላጭ ያደርገኛል። እግዚአብሔር ይርዳኝ። አሜን።” ይህን ለጳውሎስ ልምምዶች እንደመግቢያ ተጠቀሙበት። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ በወቅቱ በነበረው የአይሁድ መሪዎች ኃይማኖታዊ መማክርት ጉባኤ ፊት ቀረበ።<br>2. ጳውሎስ ስለ ትንሳኤ ስለጠቀሰ ትልቅ ሁከት ተነሳ። ገሚሶቹ በትንሳኤ ሙታን ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ ትንሳኤ ሙታን አይቀበሉትም። በዚህ ምክንያት ከፍተኛ ሁከት ተነሳ። *(23: 9)*<br>3. የጳውሎስ ሕይወት አደጋ ላይ ወደቀ። አንድ ሮማዊ አዛዥ ጳውሎስን አዳነው።<br>4. በዚያን ምሽት ጌታ በጳውሎስ አጠገብ ቆሞ አበረታው። በሮም ወንጌልን እንደሚሰብክም ነገረው።<br>5. አንዳንድ አይሁዳውያን ጳውሎስን እስከሚገድሉ ድረስ ላለመብላትና ላለመጠጣት ማሉ። ስለዚህ እንዴት እንደሚገድሉት ተማከሩ።<br>6. በአጋጣሚ የጳውሎስ የወንድሙ ልጅ ስለዚህ ሴራ ሰማ። ይህንንም ለአዛዡ አሳወቀው። አዛዡም ለጳውሎስ ልዩ ጥበቃ ተደርጎለት ወደ ቂሳሪያ እንዲሄድ ተደረገ።<br>7. ከዚያም ጳውሎስ በአገረ ገዢው ፊስጦስ ፊት ቀረበ። አሁንም ስለወንጌል ሰበከ።<br>*8. ጳውሎስ ለፊሊክስ የሰበከውን መልዕክት አተኩሩበት። በዚህ ዘመንም እንዴት ጠቃሚ አስረዱ።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው። ትምህርት ሁለትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ ለደህንነቱ ሲባል ወደ ቂሳሪያ ተወሰደ። በአገረ ገዢው ፊሊክስም ፊት ቀረበ።<br>2. በፊሊክስም ፊት ምርመራ ተካሄደበት። አይሁዳውያን ያቀረቡበት ክስ ጳውሎስ ቤተ መቅደሱን አርክሷል፣ የሕዝብ ሁከትንም ቀስቅሷል ብለው ነበር።<br>3. ጳውሎስ ለከሳሾቹ ክስ መልስ ሰጠ። ከዚያም ፌሊክስ ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ በግልጽ ሲናገር ሲሰማው እንደገና መረመረው። *(24: 24)*<br>4. ሌላ አገረ ገዢ እስኪመጣ ድረስ ጳውሎስ በእስር ቤት ለሁለት አመታት ቆየ።<br>5. ጳውሎስ እንደገና በፊስጦስ ፊት ቀረበ። የአይሁድ መሪዎችም ቀርበው ይከሱት ጀመር። ጳውሎስ ግን ወደ ኢየሩሳሌም ላለመሄድ እምቢ አለ። ለቄሳር ይግባኝ መጠየቅ እንደሚፈልግ ሲናገር ፌሊክስ ወደ ሮም እንደሚሄድ ነገረው።<br>*6. ጳውሎስ ራሱን በፊሊክስ ፊት እንደተከላከለ ተወያዩበት።*<br>*7. ፊሊክስ በጳውሎስ ስብከት እንዴት እንደንቀጠቀጠ አስቡ። (24: 25)*<br>8. *ጳውሎስ ለቄሳር ለምን ይግባኝ እንዳለና ይህ ደግሞ ምን ማለት እንደሆነ አስቡበት።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው። ጥናት ሁለትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | “የእግዚአብሔርን ተስፋ መጠበቅ” በሚል ርዕስ እንደጳውሎስ ሆናችሁ የእለት ዘገባ አዘጋጁ። | ጳውሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ስለነበረው ጽናት ግራፊቲ ፍጠሩ። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. እግዚአብሔር በምሽት ስለሰጠው ተስፋ አስቡ። ይህ ተስፋ ወደ ፍጻሜ እንዳይመጣ ሊያቆመው የሚችል ማነው? ይህ እኛን እንዴት ነው የሚያጽናናን?<br>2. ፊሊክስ ተንቀጠቀጠ። የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማትም ፈራ። *(የሐዋርያት ስራ 24: 25)* በእግዚአብሔር ቃል እንንቀጠቀጣለንን? | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. **በ2ኛ ጢሞቴዎስ 2:3** መሠረት እንደ ክርስቲያን የገጠሙንን ፈተናዎችና መከራዎች ዘርዝሯቸው። ከዚህ ዝርዝር ጋርም እግዚአብሔር እንዴት እንዳጽናናንና የመከራውን ጊዜ እንድናልፍ እንደረዳን ማስታወሻ እናዘጋጅ።<br>2. ጳውሎስ የሮማዊ ዜግነቱን ወንጌልን ለማሰራጨት ተጠቀመበት። ያሉንን መብቶች ወንጌልን ለማሰራጨት እንዴት እንጠቀምባቸዋለን? |

| | ሀ11 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ – ጳውሎስ በንጉሱ ፊት | ሀ11 - ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – የጳውሎስ መመርመር<br>ርዕስ – ቂሳሪያና ንጉስ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 25: 13-22; 26: 13-32*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** *የሐዋርያት ስራ 26: 22*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. በፊስጦስ ፊት ጳውሎስ ራሱን ተከላከሏል።<br>2. ንጉስ አግሪጳ ክርስቲያን ለመሆን ጥቂት ነው የቀረው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *የሐዋርያት ስራ 25: 13-27; 26: 1-32*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** *የሐዋርያት ስራ 26: 28*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. እግዚአብሔር በጳውሎስ ሕይወት ጣልቃ እየገባ ነው። ፊስጦስ ጳውሎስ የሞት ፍርድ በፍጹም እንደማይገባው አውቋል። አግሪጳ ደግሞ ነጻ መለቀቅ እንዳለበት አሰበ።<br>2. ጳውሎስ በግልጽ የወንጌልን መልዕክት አወጀ። አግሪጳም ክርስቲያን እንዲሆን ፈለገ። |
| *መግቢያ* | አንድ ሰው እንዴት ክርስቲያን ሊሆን እንደሚችል ተማሪዎቻችሁን ጠይቋቸው። ሰዎች ተገደው ክርስቲያኖች እንደማይሆኑ ግለጹላቸው። ሰዎችን ክርስቲያኖች እንዲሆኑ ማግባባት ጥቅሙ ምን እንደሆነ ተወያዩበት። ከልምዳችሁ በመነሳት አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በግዳጅ ሳያምኑባቸው አንዳንድ ነገሮችን ስለሚያደርጉባቸው ሁኔታዎች ምሳሌ ስጧቸው። | በክርስትና እምነታችን ሊገጥመን ስለሚችል ተቃውሞ ተነጋገሩ። ተማሪዎች ተቃውሞ ቢገጥማቸው ምንድነው የሚያደርጉት።<br>**በሉቃስ 21፡ 12 – 15** *መሠረት ለክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል ጽብረቃ አካሂዱ። እነኝህ ተስፋዎች በዚህ ጥናት እንዴት ፍጻሜ እንደሚያገኙ አስቡ።* |
| *ማጠናቀቅ* | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ በእስር ቤት ለሁለት አመታት ቆይቷል። አሁን ፊስጦስ የሚባል አዲስ አገረ ገዢ ተሹሟል። አይሁዳውያን ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም ለፍርድ እንዲልከው ይፈልጋሉ። ጳውሎስ ደግሞ የእርሱ ጉዳይ እንዲታይለት የሚፈልገው በሮም ነው።<br>2. ንጉስ አግሪጳና ሚስቱ በርኒስ ቂሳሪያ መጡ። ስለ እስረኛው ጳውሎስ መስማት ፈለጉ።<br>3. ጳውሎስ በአግሪጳ ፊት ቀረበ።<br>4. ጳውሎስ የሕይወት ታሪኩን ለአግሪጳ ነገረው። *(26: 1- 23)*<br>5. ፊስጦስ ጳውሎስ እብድ ነው አለ። አግሪጳ ግን ከጳውሎስ በሰማው ነገር ክርስቲያን ለመሆን ምንም እንዳልቀረው ተናገረ። በቄሳር ፊት ለመቅረብ ይግባኝ ባይጠይቅ ኖሮ ጳውሎስ ነጻ መውጣት እንደሚችል ሁለቱም ተስማሙ።<br>*6. ጳውሎስ በፊስጦስ ፊት ራሱን ስለተከላከለበት መንገድና ስተወሰነው ውሳኔ ትኩረት ስጡ። (26: 24-25) እንዲሁም ጳውሎስ አግሪጳ ክርስቲያን እንዲሆን እንዴት እንዳግባባው ተመልከቱ።*<br>*7. ለአግሪጳ ኑዛዜ የጳውሎስ ምላሽ ምን እንደነበረ አስቡ። (26: 29)*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።<br>ትምህርት ሶስትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ በእስር ቤት ለሁለት አመታት ቆይቷል። አሁን ፊስጦስ የሚባል አዲስ አገረ ገዢ ተሹሟል። አይሁዳውያን ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም ለፍርድ እንዲልከው ይፈልጋሉ። ጳውሎስ ደግሞ የእርሱ ጉዳይ እንዲታይለት የሚፈልገው በሮም ነው።<br>2. ንጉስ አግሪጳና ሚስቱ በርኒስ ቂሳሪያ መጡ። ስለ እስረኛው ጳውሎስ መስማት ፈለጉ። ጳውሎስ በአግሪጳ ፊት ቀረበ።<br>3. ጳውሎስ የሕይወት ታሪኩን ለአግሪጳ ነገረው። *(26: 1-23)*<br>4. ፊስጦስ ጳውሎስ እብድ ነው አለ። አግሪጳ ግን ከጳውሎስ በሰማው ነገር ክርስቲያን ለመሆን ምንም እንዳልቀረው ተናገረ። በቄሳር ፊት ለመቅረብ ይግባኝ ባይጠይቅ ኖሮ ጳውሎስ ነጻ መውጣት እንደሚችል ሁለቱም ተስማሙ።<br>*5. ጳውሎስ በፊስጦስ ፊት ራሱን ስለተከላከለበት መንገድና ስተወሰነው ውሳኔ ትኩረት ስጡ። (26: 24-25) እንዲሁም ጳውሎስ አግሪጳ ክርስቲያን እንዲሆን እንዴት እንዳግባባው ተመልከቱ።*<br>*6. ለአግሪጳ ኑዛዜ የጳውሎስ ምላሽ ምን እንደነበረ አስቡ። (26: 29)*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።<br>ጥናት ሶስትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | "ለማመን ጥቂት የቀረው" በሚል ርዕስ የቤተ ክርስቲያን ፖስተር አዘጋጁ። | በጥናቱ ላይ ጽብረቃ አካሂዱ። ከዚያም በዚህ አረፍተ ነገር ላይ ውይይት አካሂዱ። "ከመገደድ ይልቅ ማግባባት ይሻላል።" ይህ አረፍተ ነገር ከጥናታችን ጋር እንዴት ይዛመዳል? |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. የጳውሎስ የወንጌል ስርጭት አቀራረቡ ለእኛ ምን ትምህርት ይሰጠናል? በአቀራረባችን ላይ ምን ለውጥ ማድረግ ይጠበቅብናል?<br>2. አንድ ተማሪ ሌላኛውን ክርስቲያን እንዲሆን ሲያሳምን የሚያሳይ የተማሪዎች ተግባር አዘጋጁ። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ የአይሁድ መሪዎችና የሮማውያን ባለስልጣናት ስለወንጌል መልዕክት ያላቸውን አመለካከት አነጻጽሩ። ከዚህ ሰዎች ለወንጌል መልዕክት ስለሚሰጡት ምላሽ ምን እንማራለን?<br>2. የዛሬው ትምህርት ለሌሎች ወንጌልን በምንናገርበት ጊዜ አቀራረባችን ምን እንደሚመስል ምን አስተማረን? |

| | ሀ11 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ –የመርከብ አደጋ | ሀ11 - ደረጃ 4<br>ጥናት 4 – የጳውሎስ መመርመር<br>ርዕስ – የመርከብ አደጋ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***የሐዋርያት ስራ 27: 13-14, 20-44; 28: 1-9***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***የሐዋርያት ስራ 27: 25***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. በሕይወታችን በሚገጥሙን ሁኔታዎች እግዚአብሔር ሊረዳን ቃል ገብቶልናል።<br>2. የእግዚአብሔር አላማ ሁልጊዜ ይፈጸማል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***የሐዋርያት ስራ 27: 1-44; 28: 1-10, 28-31***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***የሐዋርያት ስራ 27: 24-25***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. በሕይወታችን የሚገጥሙን ሁኔታዎች በሙሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ስር ናቸው። ስናልፍባቸውም ሊረዳን ቃል ገብቶልናል።<br>2. አንዳንዶች ወንጌልን ለመቀበል እንቢተኛ ሲሆኑና ሲቃወሙ ሌሎች የወንጌልን መልዕክት እንዲሰሙ እድል ይፈጥርላቸዋል። |
| *መግቢያ* | ማዕበል አይተው ያውቁ እንደሆነ ተማሪዎቻችሁን ጠይቋቸው። በወቅቱ ምን እንደተሰማቸውና እግዚአብሔር እንዲያድናቸው ጸልየው እንደሆነ ጠይቋቸው። ልምምዳቸውን ከጳውሎስ ልምድ ጋር እንዲያዛምዱት ጠይቋቸው። | የፍርሃትን ሀሳብ ከተማሪዎቻችሁ ጋር ተወያዩበት። እጅግ በጣም ስለፈሩበት ጊዜ ጠይቋቸው። በምን ምክንያት ነበር የፈሩት? በሚያስፈሩ ሁኔታዎች ውስጥ የእግዚአብሔር ተስፋዎችን አስቡ። (*መዝሙር 23: 4*) |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ አሁን ወደ ሮም እየተጓዘ ይገኛል። ጳውሎስ ክረምት ስለሆነ ይህን ጉዞ እንዳይጀምሩት ቢመክራቸውም የሰማው አልነበረም።<br>2. ለረጅም ቀናት የቆየ ከፍተኛ ማዕበል ነበር። አንድ ሌሊት ጳውሎስ ራዕይ ያያል። በዚህ ራዕይም በጀልባይቱ ውስጥ የነበሩት በሙሉ ምንም አይነት ጉዳት እንደማይደርስባቸው ይገነዘባል። ለሁሉም ሰዎች ነገሮች ሁሉ ልክ እግዚአብሔር እንደነገረው እንደሚሆን ነገራቸው።<br>3. በድንገትም ማልታ ወደ ሚባል ተቃረቡ። መርከቡን ወደ አጠገብ አደረሱት። ሁሉም በመርከቡ ውስጥ የነበሩ 276 ሰዎች በሰላም ደረሱ።<br>4. የማልታ ሰዎች ለነዚህ ሰዎች መልካም ሆኑላቸው። ጳውሎስም በደሴቲቱ አንዳንድ ተአምራትን አደረገ።<br>5. *በማዕበሉ ውስጥ እግዚአብሔር ጳውሎስን እንዴት እንዳጽናናውና እንዳበረታው አትኩሮት ስጡበት።*<br>6. *ክርስቲያኖች ከመከራ ነጻ አለመሆናቸውን አትኩሮት ስጡበት።*<br>*7. በሕይወት ማዕበል ውስጥ ስናልፍ የእግዚአብሔር አብሮነትና ስልጣኑ ከእኛ ጋር እንዳለ ማወቅ አለብን።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ጳውሎስ አሁን ወደ ሮም እየተጓዘ ይገኛል። ጳውሎስ ክረምት ስለሆነ ይህን ጉዞ እንዳይጀምሩት ቢመክራቸውም የሰማው አልነበረም።<br>2. ለረጅም ቀናት የቆየ ከፍተኛ ማዕበል ነበር።<br>3. አንድ ሌሊት ጳውሎስ ራዕይ ያያል። በዚህ ራዕይም በጀልባይቱ ውስጥ የነበሩት በሙሉ ምንም አይነት ጉዳት እንደማይደርስባቸው ይገነዘባል። ለሁሉም ሰዎች ነገሮች ሁሉ ልክ እግዚአብሔ እንደነገረው እንደሚሆን ነገራቸው።<br>4. አስራ አራት ቀናት ያለምግብና ያለውኃ ከቆዩ በኋላ ጳውሎስ እንዲበሉና እንዲጠጡ አበረታታቸው። ከዚያም ወደ ገላጣ መሬት እየተቃረቡ መጡ።<br>5. በድንገትም ማልታ ወደ ሚባል ወደብ ተቃረቡ። መርከቡን ወደ ወደቡ አጠገብ አደረሱት። ሁሉም በመርከቡ ውስጥ የነበሩ 276 ሰዎች በሰላም ደረሱ።<br>6. የማልታ ሰዎች ለነዚህ ሰዎች መልካም ሆኑላቸው። ጳውሎስም በደሴቲቱ አንዳንድ ተአምራትን አደረገ።<br>7. ሮም ደረሱ። ጳውሎስ በቤት ውስጥ እስረኛ ሆነ። ያንን እድልም ለሌሎች ስለጌታ ኢየሱስ ለመንገር ተጠቀመበት።<br>8. *በማዕበሉ ውስጥ እግዚአብሔር ጳውሎስን እንዴት እንዳጽናናውና እንዳበረታው አትኩሮት ስጡበት።*<br>9. *ክርስቲያኖች ከመከራ ነጻ አለመሆናቸውን አትኩሮት ስጡበት።*<br>*10. በሕይወት ማዕበል ውስጥ ስናልፍ የእግዚአብሔር አብሮነትና ስልጣኑ ከእኛ ጋር እንዳለ ማወቅ አለብን።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | ተማሪዎች ራሳቸውን ጳውሎስ እንደሆኑ እንዲያስቡ ጠይቋቸው። በችግር ውስጥ እያለፈ ላለ ጓደኛቸው ደብዳቤ እንዲጽፉ ጠይቋቸው። በዚህ ደብዳቤም እግዚአብሔር እንዴት በማዕበሉ ውስጥ አሳልፎ ሮም በሰላም እንዲደርሱ እንደረዳቸው ጠይቋቸው። ያን ልምምዳቸውንም ተጠቅመው ጓደኛቸውን እንዲያጽናኑትና እንዲያበረታቱት ንገሯቸው። | ***2ኛ ቆሮንቶስ 11: 21-33*** እና ***2ኛ ጢሞቴዎስ 4: 16-18ን አንብቡ።*** በእነኚህ ሁለት ክፍሎች ውስጥ ያሉት ሁለት ታሪኮች እንዴት እርስ በርስ እንደሚዛመዱ ተወያዩባቸው። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. የጳውሎስ መርከብ መሰባበር ታሪክ እንዴት እንደሚያስተምረንና እንደሚፈትሸን ተማሪዎቻችሁን ጠይቋቸው?<br>2. በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እግዚአብሔር በመከረና በችግር ውስጥ ያለፉ ሰዎችን ሲረዳ ከምናነብባቸው ታሪኮች ምን እንማራለን? ለምሳሌ ዮሴፍ፣ ዳንኤል ወዘተ...<br>3. እግዚአብሔር በሕይወታችን ሉአላዊነቱን የሚያሳይ ጸሎት ጻፉ። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. በጳውሎስ ሕይወት ስለሆኑ ነገሮች ጽብረቃ አካሂዱ። የእግዚአብሔር ታማኝነት በጳውሎስ ሕይወት እንዴት አንጸባራቂ እንደነበረ አስተውሉ።<br>2. "መጽናት" የሚለውን ቃል የመዝገበ ቃላት ፍቺ ፈልጉ። ይህ በጳውሎስ ሕይወት እንዴት ነበር የታየው? ተማሪዎች በዚህ ረገድ ራሳቸውን ከጳውሎስ ጋር እንዲያወዳድሩ ገፋፏቸው። |

| | ሀ12– ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 – የጳውሎስ ገድሎች<br>ርዕስ - የማይቻለው! | ሀ12 – ደረጃ 4<br>ጥናት 1– የአዳኙ ልደት<br>ርዕስ – የመልአኩ መልእክት |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***ሉቃስ 1: 5-20, 57-66***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 1: 37***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ያረጁ ጥንዶች ሲሆኑ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን በመመለስ ያለማመዳቸው ጥንዶች ናቸው።<br>2. ለእግዚአብሔር የሚሳነው ምንም የለም። | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ***ማቴዎስ 1: 18-25 እና ሉቃስ 1: 26-38***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ማቴዎስ1: 21***<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>1. የኢየሱስ ውልደት በመልአክ በትክክል የተተነበየ ሲሆን ይህም ለእጩ አባቱ ከሚያስፈልጉ ዝርዝር መረጃዎች ጋር አብሮ ተነግሮታል።<br>2. ማርያምም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ልጅ እንምትጸንስ ተነግሯታል። |
| መግቢያ | አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ጸሎታቸውን እስኪመለስ ረዘም ላለ ጊዜ ሊያስጠብቃቸው እንደሚችል ተነጋገሩበት። የዘካሪያስንና የኤልሳቤጥን ሁኔታና እንዴት ለረጅም ጊዜ የማይሆን የሚመስለው ጸሎታቸው እስኪመለስ ድረስ በትዕግስት እንደጠበቁ ግለፁ። | በአለማችን ውስጥ በዚህ ዘመን ትልቅ ዜናዎች ልክ እንደተፈጸሙ እንዴት በፍጥነት እንደሚሰራጩ አስቡ። ነገር ግን ድርጊቱ ከመፈጸሙ በፊት ስለድርጊቱ መፈጸም ማንም ሊተነብይ አይችልም። እግዚአብሔር ግን ይችላል! ዮሴፍና ማርያም ሁለቱም ከእግዚአብሔር መልዕክት መጣላቸው። ይህም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት ስለ ውልደቱ የሆነ ዝርዝር መልዕክት ነበር። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. ዘካሪያስና ኤልሳቤጥ ሁለቱም ልጆች እንዲኖሯቸው ይፈልጉ ነበር። በመካከለኛው ምስራቅ በብሉይ ኪዳን ዘመን ልጆች ያልነበሯቸው ጥንዶች ይደርስባቸው የነበረውን ነቀፋና ችግር ለተማሪዎቻችሁ ንገሯቸው።<br>2. ዘካሪያስ በመቅደስ ውስጥ እንደሚያገለግል ካህን መብቶች ነበሩት።<br>3. መልአክ ተገለጠለት። ዘካሪያስም ደነገጠ። ከዚያም መልአኩ ኤልሳቤጥ እንደምትወልድ፣ የምትወልደው ልጅም በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ እንደሚሆን፣ እንዲሁም የሕዝቡን ልብ ለጌታ እንደሚያዘጋጅ ነገረው። *(ሉቃስ 1: 17)*<br>4. ዘካሪያስ ግን ልጅ ለመውለድ እርሱም ሆነ ኤልሳቤጥ ማርጀታችን ነገረው። መልአኩም መልሶ የእግዚአብሔርን ቃል ስላላመነ ቃሉ እስኪፈጸም ድረስ መናገር እንደማይችል ነገረው።<br>5. ልጁ ሲወለድ ኤልሳቤጥ ልጁ ዮሐንስ ተብሎ መጠራት አለበት አለች። ዘካሪያስም ይህንኑ በጽሑፍ አረጋገጠላቸው። ልክ ያንን እንዳደረገ መናገር ቻለ። በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ። ዮሐንስ የሚያደርገውንም ሁሉ በመንፈስ ቅደስ ሆኖ ተነበየ።<br>6. *የጎረቤቶቻቸውን ምላሽ አስቡ። (1: 65-66)*<br>7. *በመልአኩ በኩል ለመጣው የእግዚአብሔር ቃል የኤልሳቤጥንና የዘካሪያስን ምላሽ አነጻጽሩ። ከዚህ ምን እንማራለን?*<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አንድን አጠናቁ።** | የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br><br>ውይይትና ገለጻ<br>1. ማርያምና ዮሴፍ እጮኛሞች ነበሩ። በዚህ ሁኔታ ሳሉም ማርያም ከመንፈስ ቅዱስ ወንድ ልጅ እንደምትጸንስ በመልአኩ በኩል መልዕክት መጣላት።<br>2. ዮሴፍ ይህን ሲሰማ በምስጢር እጮኛውን ማርያምን ሊተዋት አሰበ። ሆኖም በሕልም ስለልጁ ውልደት ተረዳ። ለምን እንደሚወለድና በውልደቱ ቀን ስለሚፈጸሙ ትንቢቶች በዚህ ሕህልም አማካኝነት አወቀ።<br>3. ዮሴፍና ማርያም ሁለቱም የመጣላቸውን መልእክት አምነው ተቀበሉ። ልክ በመልእኩ እንደታዘዘው ዮሴፍ ሕጻኑን ኢየሱስ ብሎ ጠራው። ምክንያቱም "ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና።"<br>4. *ሶስቱን ጥያቄዎች አስቡባቸው።*<br>*(ሀ) ለምንድነው ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በተአምር የተወለደው? ለምን እንደማንኛውም ሕጻን በተለመደው መንገድ አልተወለደም?*<br>*(ለ) ለምንድነው ማርያምና ዮሴፍ ምድራዊ ወላጆቹ እንዲሆኑ የተመረጡት? ትውልዳቸውን ተመልከቱ።* ***(ማቴዎስ 1 እና ሉቃስ 3)***<br>*(ሐ) እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደዚህች ምድር ለመላክ የመረጠበት ምክንያቱ ምን ነበር?*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>ጥናት አንድን አጠናቁ። |
| ክለሳ | "የማይቻለው ሲቻል" በሚል ርዕስ ተማሪዎች በትክክል የተፈጸሙ ነገሮችን በዝርዝር ይጻፉ። (በተለይም ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎችን ይምረጡ) እነኝህ ነገሮች ምንም እንኳን የማይሆኑ ቢመስሉም! ከእነኝህ ነገሮች ስር "እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ!" ብለው ይጻፉ። | ከዛሬው ጥናት ውስጥ ወስዳችሁ በሕይወታችሁ ልትተረጉሙት የምትችሉት ምን አለ? የጌታ የኢየሱስ መምጣት ለእኛ ምን ጠቀሜታ አለው? እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በመላክ ስላደረገው ነገር ሁሉ የምስጋና ጸሎት አዘጋጁ። ***2 ቆሮንቶስ 9: 15*** |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. ከዛሬው ትምህርት ምን ተማርን?<br>2. መላእክት በዚህ ዘመን ይገለጣሉ? ለምን? | ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?<br>1. እግዚአብሔር እናንተን ራሳችሁን ወይንም የምታውቁትን ሰው ስለአንድ ይሆናል ተብሎ ስለማይታመን ነገር ነግሯችሁ ያውቃል?<br>2. በመጽሐፍ ቅዱስ ንባባችን ውስጥ ያየናቸውና ፍጻሜን ያገኙ ስለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተተነበዩ ትንቢቶች ምንድናቸው? |

| | ሀ12– ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 - የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ውልደት<br>ርዕስ – ልዩ ተግባር | ሀ12 – ደረጃ 4<br>ጥናት 2 – የአዳኙ ውልደት<br>ርዕስ – የንጉሱ ትዕዛዝ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***ሉቃስ 1: 26-38***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 1: 38***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. *ማርያምና ዮሴፍ እግዚአብሔር በልዩ መንገድ የተጠቀመባቸው ልዩ ጥንዶች ነበሩ።*<br>2. *የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወልደት ተአምራዊ ውልደት ነበር።* | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ***ሉቃስ 2: 1-7***<br><br>ቁልፍ ጥቅስ: **ሉቃስ 2: 7**<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>1. *የሮም መንግስት ቄሳር በመባል የሚታወቁ ነገስታት ነበሩት።*<br>2. ቄሳር የሕዝብ ቆጠራ አዋጅ አወጣ። በዚህ አዋጅ ምክንያትም ማርያምና ዮሴፍ ወደ ቤተ ልሔም በሕዝብ ቆጠራው ለመቆጠር መሄድ ነበረባቸው። ይህ አንድ የብሉይ ኪዳን ትንቢት ፍጻሜ ነበር። |
| *መግቢያ* | *አንድ ሕጻን ሲወለድ መጀመሪያ የምናደርገው ለልጁ ስም ማውጣት ነበው። ኢየሱስ ብዙ ስሞች ወይንም ማዕረጎች አሉት። የኢየሱስን ውልደት ዝርዝር* **በሉቃስ 1 እና 2** *እንዲሁም* **በማቴዎስ 1 እና 2** *ተመልከቱት። አንዳንድ ስሞቹንና ማዕረጎቹን ጻፏቸው። የትኞቹን ይበልጥ ወዳዳችኋቸው? ለምን?* | በዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ንባባችን የተጠቀሱ ቦታዎችን በሙሉ ጻፏቸው። እንዲሁም የሰዎች ስሞችን ዘርዝራችሁ ጻፉ። መልሶቻችሁን እንደገና የንባብ ክፍሉን መልሳችሁ በማንበብ አረጋግጡ። |
| *ማጠናቀቅ* | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>1. *ማርያም ለዮሴፍ የታጨች ወጣት ልጃገረድ ናች።*<br>2. *መልአኩ ገብርኤል ጎበኛት። በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ እንዳላት ስትሰማ ተረበሸች።*<br>3. *ስሙ ኢየሱስ ተብሎ የሚጠራ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ መልአኩ ነገራት። የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ተብሎ ይጠራል። የአባቱን የዳዊትን ዙፋንም ይወርሳል።*<br>4. *ማርያም አሁንም ድንግል እንደመሆኗ መጠን ግራ ተጋባች። መልአኩ ግን ልጁ የሚጸነሰው በመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ገለጻላት።*<br>5. *የማርያም ምላሽ አስደናቂ ነበር። "እንደቃልህ ይሁንልኝ!"*<br>6. *መልአኩ ተገልጦላት በእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ ምገስ እንዳገኘችና ልጅ እንደምትወልድ ሲነግራት በማርያም ሀሳብ ውስጥ ሊመላለሱ ስለሚችሉ ነገሮች አስቡ።* ***ቁጥር 46 እና 47.***<br>7. *"ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም።" በሰው አእምሮ ሲታሰብ በማይቻል ሁኔታ ውስጥ ስለተወለዱ ሌሎች ሕጻናት ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመጥቀስ ተነጋገሩ። "*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት ሁለትን አጠናቁ።** | የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br><br>ውይይትና ገለጻ<br>1. *ዮሴፍና ማርያም ሁለቱም የንጉስ ዳዊት ዘር ናቸው። ስለዚህ ንጉሱ የቆጠራ ትዕዛዝ ሲያወጣ ወደ ቤተ ልሔም መሄድ ነበረባቸው።*<br>2. *ይህ ርቀት በግምት ወደ 112 ኪ.ሜ. የሚደርስና በተለይ ደግሞ ለመውለድ እየተቃረበች ለነበረችው ለማርያም አስቸጋሪ ጉዞ ነበር። ቤተ ልሔም በጊዜው በብዙ ሕዝብ ተጨናንቃ ስለነበረ በከብቶች በረት ለማረፍ ሳይገደዱ አይቀሩም።*<br>3. *ኢየሱስ እጅግ በጣም ዝቅተኛና ንጹሕ ባልሆነ አካባቢ እነዲወለድ አደረገው።*<br>4. *ልክ በነቢዩ ሚኪያስ እንደተተነበየው ኢየሱስ በቤተ ልሔም ይወለድ ዘንድ አስቀድመው ሊፈጸሙ ስለሚገባቸው ነገሮች አስቡ። ይህ ሁሉ እንዲፈጸም ማድረግ የሚችለውን የእግዚአብሔርን ኃይል አድንቁ።* ***(ሚኪያስ 5: 2)***<br>**5.** ***ዮሐንስ 3: 16 እና ገላትያ 4: 4ን አንብቡ።*** *የእነኝህ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ትርጉም አስቡ። በዚህም ሁሉም ሰው ይህን ትልቅ ክንውን እንዲረዳ ለማድረግ ያስችላል።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሁለትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | ***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***<br>1. *የመልአኩ ስም ማን ነበር?*<br>2. *ዜናውን ስትሰማ የማርያም የመጀመሪያ ምላሽ ምን ነበር?*<br>3. *ከጥቂት ጊዜ በኋላ ምን ስሜት በውስጧ ተፈጠረ? (**ቁጥር 46 እና 47**)* | ***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***<br>1. *እናንተ ካላችሁበት ስፍራ በ112 ኪ.ሜ. ያህል የሚርቅ ከተማ ስም ጥቀሱ።*<br>2. *ተማሪዎች ሳያረግዙ ያን የሚያህል ርቀት በመጓዝ እንዴት ደስ ሊሰኙ ይችላሉ?*<br>3. *ከዘመናዊ አወላለድ ጋር ሲነጻጸር ኢየሱስ የተወለደበት ሁኔታ ምን አይነት መልክ ነበረው?* |
| *ከሕይወት ጋር ማዘመድ* | ***ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?***<br>*በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተጠቀሱ ቦታዎችን ዝርዝር በትንንሽ ቡድኖች ሆናችሁ ጻፏቸው። እንዲሁም የሰዎችንም ስሞች በተመሳሳይ መልኩ ዘርዝራችሁ ጻፉ። የረሳችሁት ስም አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተመልሳችሁ ክፍሉን አንብቡት። የተጻፈውን ነገር ሁሉ ጥቅም አስቡት።* | ***ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?***<br>ከዮሴፍ እይታ አንጻር "ልትወልድ የተቃረበችው ማርያም 112 ኪ.ሜ በእግሯ ተጉዛ በበረት ውስጥ ልጃችንን ወለደች።" በሚል ርዕስ ጽሑፍ አቅርቡ። |

| | ሀ12– ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 – የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ውልደት<br>ርዕስ - ቤተ ልሔም | ሀ12 – ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – የአዳኙ ውልደት<br>ርዕስ – የእረኞቹ ጉብኝት |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***ሉቃስ 2: 1-20***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 2: 11***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ኢየሱስ በዝቅተኛና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዲወለድ የእግዚአብሔር ፈቀዱና እቅዱ ነበር።<br>2. ይሆን የነበረውን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር በበላይነት ይቆጣጠር ነበር። ዛሬም እንዲሁ ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ውጪ የሆነ አንዳችም ነገር የለም። | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ***ሉቃስ 2: 8-20***<br><br>ቁልፍ ጥቅስ: *ሉቃስ 2: 11*<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>1. እረኞቹ የእለት ተግባራቸውን ለመከወን ሲንቀሳቀሱ ነበር መልአኩ የተገለጠላቸው።<br>2. የሰሙትን ነገር አመኑ። ወዲያውም እርምጃ ወሰዱ። |
| *መግቢያ* | *ተማሪዎች በታሪክ ውስጥ የተፈጸሙ ትልልቅ ክንዋኔዎችን እንዲጠቅሱ ጠይቋቸው። የእግዚአብሔር ልጅ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ አለም መምጣት አንዱ ትልቁ ታሪካዊ ክንዋኔ ነበር። የዚህን ክፍል ክንዋኔዎች የሚያሳይ የጊዜ መስመር አዘጋጁ።* | በትንንሽ ቡድኖች ሆናችሁ ይህን ክፍል በድራማ መልክ አቅርቡት። የእረኞችን አለባበስ የሚመስል አለባበስ ለብሳችሁ ድራማውን አቅርቡት። |
| *ማጠናቀቅ* | ***የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።***<br><br>***ውይይትና ገለጻ***<br>1. የሴፍና ማርያም ሁለቱም የንጉስ ዳዊት ዘር ናቸው። ስለዚህ ንጉሱ የቆጠራ ትዕዛዝ ሲያወጣ ወደ ቤተ ልሔም መሄድ ነበረባቸው።<br>2. ይህ ርቀት በግምት ወደ 112 ኪ.ሜ. የሚደርስና በተለይ ደግሞ ለመውለድ እየተቃረበች ለነበረችው ለማርያም አስቸጋሪ ጉዞ ነበር።<br>3. ቤተ ልሔም በጊዜው በብዙ ሕዝብ ተጨናንቃ ስለነበረ በከብቶች በረት ለማረፍ ሳይገደዱ አይቀሩም።<br>4. ኢየሱስ እጅግ በጣም ዝቅተኛና ንፁሕ ባልሆነ አካባቢ እንዲወለድ አደረገው።<br>5. ኢየሱስ የተለወደው በሌሊት እንደነበር ይገመታል። በዚህ ጊዜ ከእንቅልፍ ከነቁ ጥቂት ሰዎች መካከልም እረኞች ይገኙበታል።<br>6. የአዳኙን የጌታ ክርስቶስን መለወድ ዜና ተቀበሉ።<br>7. በርካታ የሰማይ ሰራዊት እግዚአብሔርን በመዝሙር እያመሰገኑ ለእረኞቹ ተገለጡላቸው።<br>8. እረኞቹ ወደ ቤተ ልሔም ሄደው የሆነውን ነገር ለማየት ወሰኑ። ማርያምን፣ ዮሴፍንና ሕጻኑን አገኟቸው።<br>9. ያዩትን ነገር ዜና አሰራጩ። ከዚያም እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያከበሩ ተመለሱ።<br>10. *መላእክቱ በመጀመሪያ ያቀረቡትንና በዚህና በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተመዘገበውን ሰላምታ እዩት። ወጣቶቹ ጥንዶች በጉዟቸው ምን እንደተሰማቸው አስቡ።*<br>11. *ከእረኞቹ ታሪክ ምን ትምህርት ልንማር እንደምንችል ተወያዩበት።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት ሶስትን አጠናቁ።** | የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br><br>ውይይትና ገለጻ<br>1. ኢየሱስ የተለወደው በሌሊት እንደነበር ይገመታል። በዚህ ጊዜ ከእንቅልፍ ከነቁ ጥቂት ሰዎች መካከልም እረኞች ይገኙበታል።<br>2. የአዳኙን የጌታ ክርስቶስን መለወድ ዜና ተቀበሉ።<br>3. በርካታ የሰማይ ሰራዊት እግዚአብሔርን በመዝሙር እያመሰገኑ ለእረኞቹ ተገለጡላቸው።<br>4. እረኞቹ ወደ ቤተ ልሔም ሄደው የሆነውን ነገር ለማየት ወሰኑ። ልክ በመልአኩ እንደተነገራቸው ማርያምን፣ ዮሴፍንና ሕጻኑን አገኟቸው።<br>5. ያዩትን ነገር ዜና አሰራጩ። ከዚያም እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያከበሩ ተመለሱ።<br>6. *እግዚአብሔር በመልአክ በኩል በስራ ላይ ለነበሩት ለእረኞቹ ተገለጠላቸው። ተግባራችም እኛም ስንሰማራ እግዚአብሔር ሊናገረን ይችላል።*<br>7. እግዚአብሔር ለእኛ ስላደረገልን ነገር ስንሰማ ለሌሎች መናገር አለብን።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሶስትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | **የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**<br>1. መላእክት **በቁጥር** 10 ላይ ባለው መልኩ ሰዎችን ሰላም የሚሉት ለምንድነው?<br>2. ዛሬም እግዚአብሔር ልክ ለእረኞቹ እንደተናገረው አይነት በመላዕክት በኩል ተራ ሰዎችን ይናገራል ትላላችሁ? ለምን?<br>3. በማርያም ሐሳብ ውስጥ ምን ይመላለስ እንደነበር ማሰብ ትችላላችሁ? ***(ቁጥር 19)*** | **የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**<br>1. ልክ መልአኩ ትቷቸው እንደሄደ ወዲያውኑ የተወለደውን ሕጻን ለማየት የሄዱት ለምን ነበር ትላላችሁ?<br>2. እረኞቹ ፈጥነው ስላደረጉት ነገር ተባረኩ። ቁጥር 20ን በዘመናዊ ቋንቋ ግለፁት።<br>3. በማርያም ሐሳብ ውስጥ ምን ይመላለስ እንደነበር ማሰብ ትችላላችሁ? ***(ቁጥር 19)*** |
| *ከሕይወት ጋር ማዘመድ* | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ራሳችሁን እንደእረኞቹ ቁጠሩ። **ከቁጥር 8 – 17** ድረስ ያለውን ክፍል ተጠቅማችሁ ስለሰማችሁት፣ ስላያችሁትና ስለተሰማችሁ ስሜት ማስታወሻ አዘጋጁ። | እግዚአብሔር የተናገራችሁን ነገሮችና መቼ እንደተናገራችሁ የምትጽፉበት ማስታወሻ አዘጋጁ። ይህ እግዚአብሔር ምን እንደተናገራችሁ እያስታወሳችሁ የምትጽናኑበት ይሆንላችኋል። |

<table>
<tr><th></th><th>ሀ12– ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 – የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ውልደት<br>ርዕስ – በመቅደሱ ውስጥ</th><th>ሀ12 – ደረጃ 4<br>ጥናት 4 – የአዳኙ ውልደት<br>ርዕስ – የጠቢባኑ ስጦታ</th></tr>
<tr><td></td><td>የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ሉቃስ 2: 22-40<br><br>ቁልፍ ጥቅስ፡ ሉቃስ 2: 30<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>1. ስምዖንና ሀና በኢየሱስ መወለድ ደስ አላቸው። ይህም የኢየሱስ መወለድ ትርጉም ስለገባቸው ነው።<br>2. እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን ወደዚህች አለም ስለላከው ልናመሰግነው ይገባናል።</td><td>የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ማቴዎስ 2: 1-23<br><br>ቁልፍ ጥቅስ፡ ማቴዎስ 2: 11<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>1. ጠቢባኑ ሰዎች ምንም እንኳን ውድ ስጦታዎችን ይዘው ቢመጡም እውነተኛው ውድ ስጦታ ግን ኢየሱስ ነበር።<br>2. እነኝህ ሰዎች ኢየሱስ ልዩ እንደነበር አውቀው ነበር።</td></tr>
<tr><td>መግቢያ</td><td>ሕጻን ልጅ ሲወለድ ስለሚፈጠረው የደስታ ድባብ አስቡ። የኢየሱስን ውልደት ልዩ የሚያደርገው ምንድነው? የአይሁድ ሕግ ልጆች ሲወለዱ ወደ ቤተ መቅደስ እንዲሄዱ በዚያም ስም እንዲያወጡለት፣ እንዲያስረዙትና ለእናትዬው መንጻትና ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚሆን መስዋዕትን እንዲያቀርቡ ይጠይቃል። (ሌዋውያን 15)</td><td>ሕጻን ልጅ ሲወለድ ስለሚፈጠረው የደስታ ድባብ አስቡ። የሕጻኑ ዘመዶችና የቤተሰቡ ወዳጆች ሕጻኑን ለመጎብኘት ከያሉበት ይሰበሰባሉ። ጠቢባኑንና ያደረጉትን ረጅም ጉዞ ለተማሪዎቻችሁ አስተዋወቁ። በዚህ ታሪክ እንደሚታየው እግዚአብሔር ሁልጊዜም ከሰይጣን ቀድሞ እንደሚገኝ ተመልከቱ። ከክፍሉ ለዚህ የሚሆኑ ምሳሌዎችን ዘርዝሩ።</td></tr>
<tr><td>ማጠናቀቅ</td><td>የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br><br>ውይይትና ገለጻ<br>1. ኢየሱስ ከተወለደ በኋላ በኢየሩሳሌም ወደ ሚገኘው ቤተ መቅደስ ተወሰደ።<br>2. ማርያምና ዮሴፍ የተወለደውን ሕጻን ኢየሱስ ብለው መሰየም እንዳለባቸው ተነግሯቸዋል። ይህንንም አደረጉት! ሕጉ በሚያዘው መሠረትም መስዋዕት አቀረቡ።<br>3. ጌታ ክርስቶስን ሳያይ እንደማይሞት በእግዚአብሔር ቃል የተገባለትን ስምኦንን በመቅደሱ ውስጥ አገኙት።<br>4. ሕጻኑን አቀፈው። አዳኙ እንደሆነም ስላወቀ እግዚአብሔርንም አመሰገነ።<br>5. ከዚህ በተጨማሪም ሃና ተብላ የምትጠራዋን በእድሜ የገፉች ነቢይት በመቅደሱ ውስጥ አገኟት። እግዚአብሔርንም እያመሰገነች “የኢየሩሳሌምንም ቤዛ ለሚጠባበቁ ሁሉ” ስለዚህ ሕጻን ትነግራቸው ነበር።<br>6. ኢየሱስ ልዩ ሕጻን እንደሆነ ስምዖንና ሐና እንዴት አወቁ?<br>7. ስለ ኢየሱስ የተናገሩት ሁሉ እንደሚፈጸም አስቡ። (ቁጥር 31-32, 34, 35, እና 38)<br><br>ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።<br>ጥናት አራትን አጠናቁ።</td><td>የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br><br>ውይይትና ገለጻ<br>1. ጠቢባኑ በምስራቅ አዩ። ኮከቡን ካጠኑ በኋላም አዲስ ንጉስ እንደሚወለድ አወቁ። ለዚህ አዲስ ለሚወለደው ንጉስ ለመስገድም ፈለጉ።<br>2. በኢየሩሳሌም ቤተ መንግስት ውስጥ ወዳለው ወደ ንጉስ ሄሮድስ መጡ። የተወለደው አዲሱ ንጉስ በዚያ ይገኝ ብለው አስበው ስለነበረ ወደ ሄሮድስ መጡ።<br>3. ሄሮድስ ተቀናቃኝ እንደመጣበት አስቦ ታወከ። ነገር ግን የኃይማኖት መሪዎች ሕጻኑ የሚወለደው በቤተ ልሔም እነደሆነ ነገሩት። (ሚክያስ 5፡2)<br>4. ጠቢባኑ ቤተ ልሔም ደረሱ። ሕጻኑን አገኙት። ውድ ስጦዎቻቸውንም ሰጡት። ሰገዱለትም።<br>5. በሕልማቸውም በሌላ መንገድ ወደ መጡበት እንዲመለሱና ስላዩት ነገር ለሔሮድስ ምንም እንዳይነግሩት እግዚአብሔር ተናገራቸው።<br>6. ዮሴፍ ሕጻኑንና እናቱን ወደ ግብጽ ይዞ እንዲሄድና ከሚመጠው አደጋ እንዲድኑ እግዚአብሔር ተናገረው። .<br>7. ሔሮድስ ጠቢባኑ ሰዎች እንዳታለሉት ገባው። ሁሉም በቤተ ልሔም ያሉና እድሜያቸው እስከ ሁለት አመት የሚደርሱ ሕጻናት እንዲገደሉ ትዕዛዝ አወጣ።<br>8. ከጥቂት ጊዜ በኋላም ዮሴፍ ወደ ናዝሬት መመለስ እንደሚችል በጌታ ተነገረው።<br>9. እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ከብዙ አመታት በፊት እንዳቀደና በነቢያቱ አማካኝነት እንዳሳወቀ አስቡ። ቁጥር 5-6, 15, 17-18, እና 23)<br>10. ሔሮድስም የሰይጣንን ስራ እንዴት እንደሰራ አስቡ።<br><br>ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።<br>ጥናት አራትን አጠናቁ።</td></tr>
<tr><td>ክለሳ</td><td>ስምኦን እርሱ ብርሃን ነው አለ። በትንንሽ ድኖች/በጥንዶች ብርሃን ስለሚሰጣቸው ጥቅሞች ተነጋገሩ። አሁን ቁጥር 32ን ለየት አድርገው ሊያዩባቸው የሚችሉባቸው መንገዶች ምንድናቸው?<br>እግዚአብሔር ይበልጥ ብርሃኑን ወደ ሕይወታቸው እንዲልክ እንዲጸልዩ አበረታቷቸው። እገዛ የሚፈልጉባቸውን ጉዳዮች እንዲያስቡና በእነኝህ ጉዳዮች እንዲጸልዩባቸው አሳስቧቸው።</td><td>ለኢየሱስ የተሰጡ ስጦታዎችን አስቧቸው። ወርቅ ንጉስ መሆኑን ይመሰክራል። ከርቤ ስቃያችንን የሚቀበለው አዳኝ መሆኑን ይመሰክራል። እጣን ሊመለክና ሊሰገድለት የሚገባ ንጉስ መሆኑን ያሳያል። ኢየሱስ ውድ ስጦታ የሚሆንባቸውን ልዩ ልዩ መንገዶችን አስቡ። እንደጌታና እንደአዳኝ ለሚቀበሉት ሁሉ ነጻ ስጦታ ነው።</td></tr>
<tr><td>ከሕይወት ጋር ማዘመድ</td><td>ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?<br>1. ከዛሬው ትምህርት በሕይወታችን ልንተገብረው የምንችለው ምን ትምህርት ቀሰምን?<br>2. ድነት ማለት ምልዓት ማለት ነው። የአንድ ጊዜ ድርጊት ሳይሆን በዕድሜ ዘመን ሁሉ የሚሆን ሂደት ነው።</td><td>ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?<br>1. ዛሬ ለጌታ ለኢየሱስ ይዘንለት መምጣት ስለምንችለው ስጦታ አስቡ።<br>2. ሰይጣን አሳሳች/አታላይ መሆኑን የሚያሳዩ የየዕለት ምሳሌዎችን ጥቀሱ። የእርሱን ስራ በጥንቃቄ እዩት።</td></tr>
</table>

***ለመምህራን የእርማት መመሪያ***

***ለደረጃ 3 ትምህርቶች***

- *ተማሪዎቹ መጽሐፍ ቅዱስን ሳያነቡ ትምህርቶቹን ማጠናቀቅ አይችሉም። ስለዚህ አንድ ወይንም ከዚያ በላይ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባቦችን ማድረግ ይጠበቅባቸው ይሆናል።*
- *ጥያቄዎቹ የተለያዩ ናቸው። እነኝህም cross words እና word grids, እንዲሁም የጎደሉ ቃላትን መሙላት ወዘተ… ናቸው።*
- *ጥያቄዎቹ የተለያዩ አይነቶች የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትሞችን በማንበብ እንዲመለሱ ታስበው የተዘጋጁ ጥያቄዎች ናቸው።*
- *የእኛ አላማ ሁሉም ተማሪዎች የትኛውንም አይነት የመጽሐፍ ቅዱስ እትም ተጠቅመው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ መርዳት ነው።*
- *በየሳምንቱ 20 ነጥቦች ይሰጣቸዋል። በወር ደግሞ ትምህርቶቹ በሙሉ ትክክል ከሆኑ በአጠቃላይ 80 ማርኮች ይሰጣቸዋል።*
- *ደረጃ 3 - ለአንድ መልስ አንድ ማርክ ብቻ ይሰጠዋል።*

***ደረጃ 4 ጥናቶች***

- *እነኝህ በደረጃ ሶስት ከሚሰጡት ትምህርቶች በትንሹ ጠጠር ይላሉ።*
- *ተጨማሪ ውስብስብ ጥያቄዎችና መልሶች ያስፈልጋሉ።*
- *በሳምንት ሀያ ነጥቦች በወር ደግሞ 80 ነጥቦች ይሰጣሉ። ይህም ትምህርቶቹ በሙሉ ትክክል ሲሆኑና ጥያቄዎቹ የተሟላ መልስ ሲኖራቸው ነው።*

***የነጥብ አሰጣጥ ፍንጮች***

*መምህራን በመጀመሪያ የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ።*

- *እያንዳንዱን ትምህርት መገምገምና መልሶቹ ትክክል መሆን አለመኖናቸውን ምልክት ማድረግ።*
- *በመመሪያው መሰረት ትክክለኛውን ነጥብ መስጠት።*
- *ነጥብ ስንሰጥ የተለያየ አይነት ቀለም ያላቸውን ብዕሮች /እስክርቢቶዎች/ መጠቀም አለበን። ትክክል ለሆኑ መልሶች የ "✓" ምልክት እናድርግ።*
- *ትክክል ላልሆኑ መልሶች ትክክለኛ መልሶቻቸውን አስቀምጡ። የፊደላት ግድፈቶች ካሉም እርማት ስጡ። ለፊደላት ግድፈት ነጥብ አይቀነስም።*
- *በከፊል ትክክል ለሆኑ መልሶች ነጥብ ቀንሱ።*
- *የወሩን ድምር ነጥብ አስቀምጡ። ይህንንም በጀርባ ገፅ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ለይ ጻፉ።*

*አንዳንዴ በአግባቡ ሊጋስ መሆን ያስፈልጋል። እንዲሁም ተማሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱን ማጠናቀቅ እንዲችሉ ለማበረታታት ማንኛውንም ነገር ማድረግ አስፈላጊ ነው። በየወሩ መጨረሻ መምህራን አንድ የማበረታቻ ቃል ለተማሪዎች ቢፅፉ መልካም ነው። ይህን ለማድረግም በየትምህርቶቹ ቦታ ተዘጋጅቷል። ጥሩ የቀለም ቅብን፣ ንፅሕናን፣ ተማሪው ያስመዘገበውን ነጥብ፣ ተማሪው ምን ያህል እንደተረዳ የሚገልፁ አስተያየቶችን መጻፍ ይቻላል።*

*አስተያየቶች በተቻለ መጠን የተለያዩ እንዲሆኑ መጣር አለብን። ጥያቄዎች፣ አረፍተ ነገሮች፣ ምልከታዎች፣ ማበረታቻዎች ወዘተ…ይህን ልዩነት ለማሳየት ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ይህ በጥልቅ ማሰብንና የተማሪዎች ፍላጎት መጠበቁን ማረጋገጥ ይጠይቃል። አንድ አረፍተ ነገር ወይንም ደግሞ ጥያቄ በየወሩ የሚደጋገም ከሆነ የሚፈለገውን ግብ ላይመታ ይችላል።*

***ደረጃ 3***

***አጠቃላይ አስተያየቶች***

*"በጣም ጥሩ ስራ! ጥያቄዎቹን በጥንቃቄ እንዳነበብካቸው ያስታውቃል። በተለይም ለመጨረሻው ጥያቄ የሰጠኸው መልስ አስደስቶኛል። ትክክለኛ ቃላትን ተጠቅመሃል።"*

*"ሃይ ዮናታን! ሰለጥረትህ አመሰግንሃለሁ። ሁሉንም ጥያቄዎች ለመመለስ መሞከርህ ትልቅ ነገር ነው። ያልሰራሃቸውን እኔው አሟልቼልሃለሁ።"*

***መንፈሳዊ አስተያየቶች***

*"ከእስራኤል ልጆች ጋር ሙሴ አስቸጋሪ ጊዜ ነበረው። ሆኖም እግዚአብሔር ሙሴ በራሱ ለነገሮች መፍትሔ እንዲፈለግ ብቻውን አልተወውም።"*

*"ዮሴፍ አባቱ እግዚአብሔርን እንዲወድ ያስተማረውን ትምህርት ፈፅሞ አልረሳውም። ከቤተሰቦቹ በጣም ርቆ በነበረበት ጊዜ እንኳን ይህን ፍፁም አልረሳውም።"*

*"በርጠሎሜዎስ ጌታ ኢየሱስን ለመንካት ቆርጦ ነበር። ማየት ችሏልና ምንም አይቆጨውም። አሁን ለእርሱ ጌታ ኢየሱስ ማለት በጣም ልዩ የሆነ ሰው ነው።"*

***ደረጃ 4***

***አጠቃላይ አስተያየቶች***

*"ሌላ በጣም አስገራሚ ትምህርት! የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮቹን በሚገባ የተረዳሃቸው ይመስላል። እነኝህ ታሪኮች እንዳሰደሰቱህም ተስፋ አደርጋለሁ። ትምህርቶችህን በጥንቃቄ ስላጠናሃቸው በጣም አመሰግንሃለሁ። በፍጥነት ልትጨርሳቸው ትችላለህ። ስለዚህ ጥረትህን በሙሉ አደንቃለሁ።"*

*"ራሔል! በጣም ጥሩ ሙከራ! መልሶችሽን አይቻቸዋለሁ። ታሪኩን ሙሉ በሙሉ የተረዳሽው አይመስልም። ምናልባት እንደገና ማንበብ ይጠበቅብሽ ይሆናል።"*

***መንፈሳዊ መልእክቶች***

*"ምሳሌዎች አንዳንድ ጊዜ ሰማያዊ ወይንም ጥልቅ ትርጉም በውስጣቸው የያዙ ምድራዊ ታሪኮች ተብለው ይጠራሉ። በጥናት 3 ያለውን ምሳሌ ጥልቅ ትርጉም ምን እንደሆነ ልታስበው ትችላለህ?"*

*"እስጢፋኖስ በጭካኔ አገዳደል ሞተ። ሆኖም ሞትን አልፈራም። ምክንያቱም አሁንም እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በበላይነት እንደሚቆጣጠር ያውቅ ስለነበር ነው። እንዲሁም ቢሞትም እንኳን በሰማይ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንደሚሆን ያውቅ ነበር።"*

© የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት 2007ዓ.ም.

www.besweb.com

በሕግ የተመዘገበ የዩ.ኬ ለጋሽ ድርጅት 1096157